# ክብረ ድንግል ማርያም

«መልአኩም ወደ እርስዋ ገብቶ፦ ደስ ይበልሽ፣ ጸጋ የሞላብሽ ሆይ፣ እግዚአብሔር ካንቺ ጋር ነው» አላት (ሉቃ. 1፥28)

ድንግል ማርያም ፍጹም አምላክ የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን በመውለድዋ ክብርት ናት። ክብርዋም ከቅዱሳን ሁሉ በላይ ነው። የቅድስት ድንግል ማርያም ክብር ከሦስት ወገን ነው። ይኸውም፤

1ኛ. የክብር ባለቤት ከሆነው ከእግዚአብሔር፣
2ኛ. ከቅዱሳን መላእክትና ከሊቃነ መላእክት፣
3ኛ. ከሰው ልጆች ወገን ነው።

## ሀ. በእግዚአብሔር በኩል መከበር

ሊቀ መላእክት ቅዱስ ገብርኤል ወደ ድንግል ማርያም ቀርቦ «ጌታ እግዚአብሔር ካንቺ ጋር ነው» ያላት የክብር ባለቤት እግዚአብሔር ከዓለም ሴቶች መካከል ሰለ መረጣትና የአምላክ እናት እንድትሆን ስላደረጋት ነው። መልአኩ ማርያምን «አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ» ማለቱ ድንግል ማርያምን ከከበሩ ሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ ሲላት ነው። ይኸውም የበለጠ ክብርና የበለጠ በረከት ያላት መሆኑን ያመለክታል።

እንደሚታወቀው፣ ከድንግል ማርያም ፊት በራሱ በእግዚአብሔር የተናገራቸውና በመላእክትም የተበሰሩ ብዙ ሴቶች እንደ ነበሩ መጽሐፍ ቅዱስ ያረጋግጣል። ለብዙ ዓመታት መካን ሆና ትኖር የነበረችው የአብርሃም ሚስት ሣራ ልጅ እንደምትወልድ በአብርሃም አማካይነት እግዚአብሔር ነገራት (ዘፍጥ.18፥ 9-15)። ነገር ግን ሣራ ከሴቶች መካከል የተባረከች መሆንዋን፣ የእግዚአብሔር ጸጋ የሞላባት መሆንዋን እግዚአብሔር አልነገራትም። ኤልሳቤጥ ወንድ ልጅ እንደምትጸንስለትና እንደምትወልድ በቤተ መቅደስ ባበሰረው ጊዜ የክብርና የልዕልና ቃል ጨምሮ የነገረው ቃል የለም (ሉቃ.1፥8-20)።

ስለዚህ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያምን ግን እግዚአብሔር ሰለ መረጣት ከሁሉ በላይ የከበረች ናት። እግዚአብሔርም ሰላከበራት፣ የእግዚአብሔር እናት ለመሆን በቃች፤ ድንግል፣ ንጽህት ሆና ሰለ ተገኘችም የአምላክ እናት ለመሆን ቻለች፤ የአምላክ እናት በመሆንዋም ሊቃነ መላእክትና መላእክት አከበሩአት።

## ለ. በመላእክት ዘንድ መከበር

መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ወደ ድንግል ማርያም በተላከ ጊዜ ወደ እርስዋ ገብቶ ከፍ ባለ አክብሮት «ደስ ይበልሽ ጸጋ የሞላብሽ ሆይ፣ እግዚአብሔር ካንቺ ጋር ነው፤ አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ» አላት። ይህ ቃለ ብሥራት ከዚያ በፊት ለማንም ያልተነገረና ማንም ሰው ያልሰማው ነው። ሰለዚህ በዚህ ቃለ ብሥራት አማካይነት ድንግል ማርያም እግዚአብሔር ከእርስዋ ጋር የሆነ፣ ጸጋ እግዚአብሔርም የሞላባት፣ ከሴቶች መካከልም የተባረከች ሰለ ሆነች ይህን ሁሉ ክብር ያገኘችው ከራሱ ከእግዚአብሔር መሆኑን እንረዳለን።

ቀጥሎም መልአኩ የአምላክ እናት ለመሆን ከእግዚአብሔር ልዩ ጸጋ ማግኘትዋን ሲያረጋግጥላት «ማርያም ሆይ በእግዚአብሔር ፊት ጸጋን አግኝተሻልና አትፍሪ። እነሆም ትጸንሻለሽ፤ ወንድ ልጅንም ትወልጂለሽ፤ ሰሙንም ኢየሱስ ትይዋለሽ። እርሱም ታላቅ ይሆናል፤ የልዑል ልጅም ይባላል። ጌታ አምላክም የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል። በያእቆብም ቤት ለዘላለም ይነግሣል፤ ለመንግሥቱም መጨረሻ የለውም»አላት (ሉቃ. 1፥30-34)።

እስዋ ግን ፍጹም ድንግል ናትና መልአኩ የመጸነስንና የመውለድን ነገር አንስቶ በነገራት ጊዜ «እኔ ወንድ ስለማላውቅ ይህ እንዴት ይሆናል?» አለችው። መልአኩም «ወንድ ሰለማላውቅ ይህ እንዴት ይሆናል

?» ብላ ስለ ጠየቀችው ሲመልስ «መንፈስ ቅዱስ ባንቺ ላይ ይመጣል፤ የልዑል ኃይልም ይጸልልሻል፤ ሰለዚህ ደግሞ ካንቺ የሚወለደው ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል» አላት (ሉቃ. 1፥35)።

ይህ ዓይነት ብሥራትም ሆነ ታሪክ ከድንግል ማርያም በፊት የነበረው የሰው ልጅ ሙሉ ፍጹም አይታወቅም ነበር። እንደሚታወቀው በሕገ እግዚአብሔር (ዘፍጥ.1፥28) ሴት ልጅ መጸነስና መውለድ የምትችለው በወንድ ምክንያት ነው። ስለዚህ በድንግልና ጸንታ ለነበረችው ድንግል ማርያም ያለ ወንድ መጸነስና መውለድ ፈጽሞ የማይሆንና የማይታሰብ ነው። በዚህ ምክንያት ድንግል ማርያም «ይህ እንዴት ይሆናል? » ያለችው ሰለዚህ ነው።

በእርግጥ ልዑል እግዚአብሔር ዓለሙን ለማዳን ሲል በድንግል ማርያም ላይ የፈጸመው ታላቅ ምስጢር በሰው አእምሮ አይታወቅም፤ በፍጡራን ጥበብም አይመረመርም። ይኸውም መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል «ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና» ሲል እንደ ተናገረው (ሉቃ. 1፥35)፣ ድንግል በድንግልና እንድትጸንስና ሰማይና ከሰማያትም በላይ ያለው ሰማይ ሊሸከመው የማይችል ኃያል አምላክ (ነገስ. ቀዳ. 8፥27) ከድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍስዋ ነፍስ ነስቶ ያለ መለወጥ ሰው እንዲሆን ማድረግ ለእግዚአብሔር አልተሳነውም። ሰለዚህም አካላዊው ቃል ወልድ እግዚአብሔር ሰው ሆነ (ዮሐ. 1፥14)። በመሆኑም ይህ የማይመረመር ታላቅ ምስጢር ለተፈጸመላት ለቅድስተ ቅዱሳን ድንግል ማርያም ታላቅ የክብር ክብር ተሰጥቷታልና ሰለዚህ እናመሰግናታለን። በእግዚብሔር ፊት ጸጋን (ሞገስን) ማግኘት፣ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ መሆን፣ የአምላክ እናት መሆን ፣ ለቅድስተ ቅዱሳን ድንግል ማርያም ብቻ የተሰጠ የተደራረበ ልዮ ጸጋ ነው። ከሁሉም በፊት በጸጋ ላይ ጸጋ የተሰጣት እስዋ ብቻ ናት (ዮሐ. 16፤ 17)። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «በጎ (መልካም) ሥራ ላላቸው ምስጋናና ክብር፣ ሰላምም ይሆንላቸዋል» ሲል እንዳሰተማረው (ሮሜ. 2፤10) ትህትናን ከንጽህና፣ ድንግልናን ከቅድስና አሰተባብራ፣ ይዛ ለተገኘች ለቅድስተ ቅዱሳን ድንግል ማርያም ክብርና ምስጋና ይገባታል።

## ሐ. በሰው ልጆች ዘንድ መከበር

ቅድስተ ቅዱሳን ድንግል ማርያም በእግዚአብሔር ዘንድ እጅግ የከበረችና የተወደደች እንደ ሆነች ሁሉ በሊቃነ መላእክትና በመላእክትም ክብርት፣ ልዕልት፣ ቅድስት ናት። ሰለዚህም በሰውና በሰው ልጆች ዘንድ የከበረችና የተመሰገነች ናት።

በቅዱስ ወንጌል እንደምናነበው ቅድስተ ቅዱሳን ድንግል ማርያም አምላክ ወልድ አምላክ የሆነውን አካላዊ ቃልን በንጽህና፣ በድንግልና እንደምትጸንስና እንደምትወልድ በብርሃናዊው መልአኩ በቅዱስ ገብርኤል ከተበሰረች በኋላና፣ በመልአኩ የተነገረውም ምስጢር ከተፈጸመላት በኋላ ቅድስት ኤልሳቤጥን ለማየት ወደ ይሁዳ አገር ወደ ዘካርያስ ቤት ሄደች። ወደ ካህኑ ወደ ዘካርያስ ቤት ገብታም ቅዱስ ዮሐንስን ጸንሳ ለነበረችው ለቅድስት ኤልሳቤጥ የሰላምታ ጽምፅ አሰማቻት፣ ቅድስት ኤልሳቤጥም የቅድስተ ቅዱሳን ድንግል ማርያምን ድምፅ በሰማች ጊዜ መንፈስ ቅዱስ በቅድስት ኤልሳቤጥ ላይ አደረ፤ በመንፈስ ቅዱስ ተሞላች፤ በቅድስት ኤልሳቤጥ የነበረው ፅንስም በደስታ ዘለለ። በዚህ ጊዜ ቅድስት ኤልሳቤጥ በታላቅ ድምጽ ጮኻ እንዲህም አለች፦ «አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ፤ የማኅፀንሽም ፍሬ ቡሩክ ነው፤ የጌታዬ እናት (እሙ ለእግዚእየ) ወደ እኔ ትመጣ ዘንድ እንዴት ይሆንልኛል? እንሆ የሰላምታሽን ድምፅ በሰማሁ ጊዜ ፅንሱ በማኅፀኔ በደስታ ዘለለ። ከእግዚአብሔር የተነገረላት ቃል ይፈጸማልና ያመነች ብፅዕት ናት» ማለት (ከእግዚአብሔር የተነገረልሽ ቃል ይፈጸማልና ብፅዕት ነሽ) በማለት ቅድስት ኤልሳቤጥ አመሰገነቻት (ሉቃ. 1፤39-47)

ቅድስተ ቅዱሳን ድንግል ማርያም ከእግዚአብሔር ዘንድ የተሰጣትን ድርብ ጸጋ ተቀበለች፣ ከሊቀ መላእክት ቅዱስ ገብርኤል የቀረበላትን ምስጋና ሰማች። ቀጥሎም በቅድስት ኤልሳቤጥ አንደበት የተነገረላትን ምስጋና ተቀብላ እንዲህ አለች፤ «እነሆ ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል (ያመሰግኑኛል)» (ሉቃ. 1፤48-49) በማለት መልአኩ ቅዱስ ገብርኤልና ቅድስት ኤልሳቤጥ ካመሰገንዋት ጊዜ ጀምሮ፣ እርስዋም የአምላክ እናት ከሆነችበት ሰዓት አንስቶ ትውልድ ሁሉ (የሰው ልጆች በሙሉ) «ብፅዕት፣ ብርክት፣ ቅድስት» እያሉ ያመሰግኑአታል።

## መ. የቤተ ክርስቲያን አባቶች እንዳመሰገንዋት

የቅዱስ ገብርኤልን ምስጋና አብነት አድርገው ቅድስተ ቅዱሳን ድንግል ማርያም ብዙ የቤተ ክርስቲያን አባቶች አመሰግነዋታል። ከእነሱም ጥቂቶቹን ለአብነት ያህል እንጠቅላለን።

## 1. ቅዱስ ጎርጎርዮስ ገባሬ መንክራት

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ገባሬ መንክራት በትንሽዋ እስያ በተለይ ፓንቲዮስ የምትባል አገር ዋና ከተማ በነበረች ው በኒኦቂሳርያ በ205ዓ.ም ተወለደ። ለ20 ዓመታት ያህል በመጀመሪያ በፍልስፍና ከዚያ ቀጥሎ በቴኦሎ ጂ (በነገረ መለኮት) ትምህርት ቤት የሚያስፈልገውን ከፍተኛ ዕውቀት ከተማረ በኋላ በ240 ዓ.ም. የኒኦ ቂሳርያ ሀገረ ስብከት ኤጲስ ቆጶስ ሆኖ ተሾመ። ለሰብከተ ወንጌል አገልግሎት በሚዘዋወርበት ጊዜ በክር ስቶስ ስም ልዩ ልዩ ሕሙማንን በመፈወስ አሰደናቂ ተአምራትን ይፈጽም ሰለ ነበር፣ ገባሬ ተአምር (ተአ ምር ሠሪ) እየተባለ ይጠራ ነበር። በግሪክ ልሳን ታውማቱርጉስ ይሉታል፣ ገባሬ ተአምር ማለት ነው። በ2 65 ዓ.ም በአንጾኪያ መናፍቁ ጳውሎስ ሳምሳጢን ካወገዙት ኤጲስ ቆጶሳት መካከል አንዱ ቅዱስ ጎርጎር ዮስ ነበር። ቅዱስ ጎርጎርዮስ ገባሬ ተአምር በተሾመበት ሀገረ ስብከት (ኢፓርኪያ) ቅዱስ ወንጌልን እየሰ በከና ልዮ ልዮ አሰደናቂ ተአምራትን እያደረገ (እየፈጸመ) በብዙ ሺህ የሚቆጠሩትን ሰዎች የክርስቶስ ተ ከታዮች እንዲሆኑ አድርጎአል። ገባሬ መንክራት ቅዱስ ጎርጎርዮስ ሐዋርያዊ አገልግሎቱን ፈጽሞ በገድ ልና በሰማዕትነት በ270 ዓ.ም አርፎአል።

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ልዮ ጸጋ የሆነው የቅድስት ድንግል ማርያም ጣዕመ ፍቅር በምላት ያደረበት ቅዱስ ሰ ው ሰለ ነበር ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም ቅድስና ብዙ ውዳሴ ተናግሮአል። በተናገረው ብዙ ውዳሴ ጥ ቂቱን ቀጥለን እንጠቅሳለን።

«የምሕረት ዘመን በደረሰ ጊዜ መልአኩ ገብርኤል ወደ ቅድስት ድንግል ቀርቦ (ምልዕተ ጸጋ፣ ምልእተ ~ ብር ሆይ! ደስ ይበልሽ፣ እግዚአብሔር ካንቺ ጋር ነው) በተደራረበ ጸጋ በእርሷ ላይ አደረ፤ ምክንያቱም ከትውልድ ሁሉ በመንፈስም በሥጋም ንጽሕት እርስዋ ብቻ ከመሆንዋም በላይ ሁሉን ማድረግ የሚችል ጌታችንን የወለደች ናት። ሰለዚህም አድናቆትንና አክብሮትን እናቀርብላታለን። አድናቆትንና አክብሮትን የምናቀርብላት እሰዋ በአፍአ በውስጥ፣ በነፍስ በሥጋ ንጽሕት ሰለ ሆነች ነው።

«መልአኩ ከሁሉም አሰቀድሞ (ደስ ይበልሽ፣ ጸጋ የሞላብሽ ሆይ፤ እግዚአብሔር ካንቺ ጋር ነው፤ አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ) ሲል ሰላምታ (ክብር) የሰጣት የቅድስና ጌታ፣ የቅንነት ባለቤት፣ ነጻነትን የሚያድል፣ የሕይወት ጠባቂ፣ እውነተኛውን ሰላም የሚሰጥ፣ ከአፈር ሰውን የፈጠረ፣ ከሰው (ከወንድ) ጎ ንም ሔዋንን የፈጠረ አምላክ ከእርሷ ጋር ሰለሆነ ነው።

«ሰለዚህ ወንድሞች ሆይ እንዲህ ኑ በአንድ ላይ ሆነን (ምልእተ ጸጋ፣ ምልእተ ክብር ሆይ! ደስ ይበልሽ ፤ እግዚአብሔር ካንቺ ጋር ነው) የሚለው የመልአኩን ምስጋና እንዘምርላት፤ ንጽሐ ሥጋ፣ ንጽሐ ነፍስ፣ ንጽሐ ልቡና ገንዘቦችሽ የሆኑ አንቺን እግዚአብሔር ለልጁ ማደሪያ ትኾኚ ዘንድ መርጦሻል... እያልን እ ናመስግናት። በእርሱ ለሚያምኑ የሕይወት ብርሃን የሚሰጥ ጌታ ያሰገኘሽ ምልዕተ ጸጋ ሆይ! ክብርና ምስ ጋና ላንቺ ይሁን። የቅድስና ፀሐይ፣ ነውር ያልነካው የሕይወት አበባ የሆንሽ ምልዕተ ጸጋ ሆይ! ክብርና ምስጋና ላንቺ ይሁን። አንቺን ለሚያከብሩ ሰዎች ነፍስ በደስታ የምትሞይ ምልዕተ ጸጋ ሞልዕተ ክብር ሆይ! ደስ ይበልሽ፤ ገበሬ ያላረሳት የሕይወት ፍሬን ያሰገኘች ንጽሕት እርሻ አንቺ ነሽና ደስ ይበልሽ። ቃለ እግዚአብሔር ከቅዱስ ማኅጸንሽ ሥጋን ነስቶ ዳግማዊ አዳም ሆነ፤ እሱን ለመፅነስም መንፈስ ቅዱ ስ አጸናሽ፤ የልዑል ኃይልም ከለለሽ (ጋረደሽ)» በማለት ቅዱስ ጎርጎርዮስ አመስግኖአታል። (ድርሳነ ጎር ጎርዮስን ክፍል 2 ይመልከቱ)።

## 2. ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ

አራተኛው ክፍለ ዘመን ምሕረት ታላላቅ የቤተ ክርስቲያን አባቶች የተነሱበት ብርሃናዊ (ወርቃዊ) ዘመን ነበር። ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ በምድረ ሶርያ ልዮ ስሙ ንጽቢን በተባለ ቦታ በ 306 ዓ.ም ተወለደ። እስ ከ 338 ዓ.ም. ትምህርተ መለኮትንና ፍልስፍናን ሲማር፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን ሲመረምርና ሲተረጉም ኖረ ። በ 338 ዓ.ም ማዕረገ ዲቁና ተቀበለ። ቅዱስ ኤፍሬም በቅስና ወይም በኤጲስ ቆጶስነት ማዕረግ መኖር አልፈቀደም፤ ነገር ግን መላ ሕይወቱን በብሕትውናና በገድል እንዳሳለፈ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ተመዝግ ቦአል። ቅዱስ ኤፍሬም በዘመኑ የተነሱትን መናፍቃን በመገሠጽ በግጥም መልክ ብዙ መጻሕፍት እንደ ጻ ፈ በሕይወት ታሪኩ ተመዝግቦአል። ቅዱስ ኤፍሬም ቅድስት ድንግል ማርያምን በማመሰገን ብዙ ውዳሴ እንደ ደረሰ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ይመሰክርለታል።

ቅዱስ ኤፍሬም ቅድስት ድንግልን እንዲህ ብሎ አመሰግኖአታል፦ «በድንግልና ፍጽምት የሆንሽ ማርያም ሆይ፣ የድንግልናሽ ምስጋናና ክብር ታላቅ ነው፤ እግዚአብሔር ካንቺ ጋር ሰለ ሆነ ጸጋን (ባለሟልነትን) አገኘሽ። ያዕቆብ ከምድር እስከ ሰማይ ደርሳ የእግዚአብሔር መላእክት ሲወጡባት፣ ሲወርዱባት ያየት የብርሃን መሰላል አንቺ ነሽ (ዘፍጥ. 28፤11 -23)። ሙሴ በነደ እሳት ሳትቃጠል ያየት ዕጽ (ዛፍ) አንቺ ነ

ሽ፤ ይኸውም ወደዚህ ዓለም መጥቶ በማኅፀንሽ ያደረው የእግዚአብሔር ልጅ ነው፤ የመለኮቱ እሳትነት (እሳት) ቅዱስ ማኅፀንሽን አላቃጠለውም። ዘር ያልተዘራባት እርሻ አንቺ ነሽ፤ የሕይወትም ፍሬ ካንቺ ወጣ፣ ዮሴፍ የዋጀት የነበረ እንቀሩን ያገኘበት መዝገብ (ሳጥን) አንቺ ነሽ፤ ይኸውም በማኅፀንሽ ያደረው በዚህ ዓለምም የወለድሽው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

«የመላእክት ደስታቸው የሆነ ጌታችንን የወለድሽልን ሆይ፣ ደስ ይበልሽ፣ የነቢያት ዜናቸው ንጽሕት ሆይ ደስ ይበልሽ። እግዚአብሔር ካንቺ ጋር ሰለ ሆነ ጸጋን (ባለሟልነትን) አግኝተሻልና ደስ ይበልሽ፤ የዓለሙ ሁሉ ስው ደስታ የሆነ የመልአኩን ቃል (ብሥራት) ተቀብለሻልና ደስ ይበልሽ፤ ዓለሙን ሁሉ የፈጠረ ጌታችንን የወለድሽልን ሆይ! ደስ ይበልሽ፤ በሚገባ (በእውነት) የአምላክ እናት ተብለሻልና ደስ ይበልሽ፤ የሔዋን መድኃኒት ሆይ! ደስ ይበልሽ፤ በሚገባ (በእውነት) የአምላክ እናት ተብለሻልና ደስ ይበልሽ፤ የሔዋን መድኃኒት ሆይ! ደስ ይበል፤ ፍጥረቱን ሁሉ የሚመግበውን እሱን ጡትሽን አጥብተሽዋልና ደስ ይበልሽ፤ የሕያዋን (የጻድቃን) ሁሉ እናታቸው ቅድስት ሆይ፤ ደስ ይበልሽ» (ከማክሰኞ ውዳሴ ማርያም የተጠቀሰ)።

የዕለቱ ተከፍሎ በሚጸለየው ውዳሴ ማርያም ቅዱስ ኤፍሬም ቅድስት ድንግልን ድንቅ በሆነ ምሳሌ እየመሰለ አመስግኖአታል። ከፍ ብለንም እንደ ተመለከትነው የቅዱስ ገብርኤልን አርአያ (አብነት) ተከትሎ አመሰግኖአታል፤ እንዲህ ብሎ፦ «አሕዛብ ሁላችሁ ኑ፣ ማርያምን እናመስግናት፤ እናትና ድንግልን ሁለቱንም ሆናለችና። ርኩስት የሌለብሽ፣ የአብ ቃል መጥቶ ካንቺ ፍጹም ሰው የሆነ ንጽሕት ድንግል ሆይ! ደስ ይበልሽ፤ ነውር የሌለብሽ ፍጽምት፣ ጉድፍ የሌለብሽ ሙዳይ ሆይ! ደስ ይበልሽ፤ ለቀደመው ሰው አዳም ሁለተኛ አዳም የሆነ የክርስቶስ ማደሪያ የሆንሽ የምትነገሪ ገነት ሆይ! ደስ ይበልሽ፤ ከአባቱ ከአብ ያልተለየ ወልድ ዋህድ እሱን የተሸከምሽ ሆይ! ደስ ይበልሽ፤ በክብር ጌጥ ሁሉ ያጌጠ እርሱ መጥቶ ሰው የሆነብሽ ንጽሕት የሠርግ ቤት ሆይ! ደስ ይበልሽ፣ የመለኮት እሳት ያላቃጠለሽ ዕፀ ጳጦስ ሆይ! ደስ ይበልሽ፣ በኪሩቤል ላይ የሚቀመጠውን ሰማያዊ አምላክን በሥጋሽ የተሸከምሽ፣ አገልጋይ፣ እናት፣ ድንግልና ሰማይ ሆይ! ደስ ይበልሽ.....» (ከሮብ ውዳሴ ማርያም የተወሰደ)።

<u>3. ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ</u>

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ከታላላቅ የቤተ ክርስቲያን መምህራን ከፍተኛውን የክብር ቦታ ከያዙ አበው መካከል አንዱ ነው። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በሶርያ በአንጾኪያ ከተማ አካባቢ በ344 ዓ.ም ተወለደ። በ381 ዓ.ም በሊቀ ኤጲስ ቆጶስ መሊትዮስ እጅ በአንብሮተ እድ ዲቁና ተሾመ፤ በ386 ዓ.ም ደግሞ በአንጾኪያው ሊቀ ኤጲስ ቆጶስ ፍላቪያን ቅስና ተቀበለ። ቅዱስ ዮሐንስ በትርጓሜ መጻሕፍትና በነገረ መለኮት እጅግ ከፍ ያለ ዕውቀት ያለው አባት ነበር። በስብከተ ወንጌል በኩል ደግሞ ልዩ ጣዕመ ቃልና ጥልቅ ምስጢር የታደለ ሰለ ነበር በጣዕመ ስብከቱ የተመሰጡ ምእመናን «አፈወርቅ» (ክሪሶስቶሞስ) ብለው ሠይመውታል።

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በስጊድና በጸሎት ታላቅ መስተጋድል አባት ሰለ ነበር በሕዝበ ክርስቲያኑና በቤተ መንግስቱ ምርጫ እሱ ሳይፈቅስ በግድ በ398 ዓ.ም የቁስጥንጥንያ ፓትርያርክ ሆኖ ተሾመ። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እውነተኛ ኖላዊ (ቸር ጠባቂ) ሰለነበር፣ «ፍርድ ጎደለ፤ ድሃ ተበደለ» እያለ በማስተማሩ ከንግስት ኤብዶክስያና ከተከታዮችዋ ጋር ሊስማማ አልቻለም። በዚሁ ምክንያት ከንጉሡ ነገሥት ኤርካድያ ጋርም ተጣላ። ሰለዚህ የተወሰኑ የቤተ መንግሥቱን ሐሳብ የሚደግፉ ኤጲስ ቆጶሳት የንግሥቲቱ መሣሪያ ሆነው በሃያ ዘጠኝ የሐሰት ነጥቦች ከሰሱት፤ ከዚያም በ404 ዓ.ም አውግዘው ለስደት ዳረጉት። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ከመንበረ ፓትርያርክ በወታደር ኃይል ተገዶ ካቭካዝ ወደ ተባለ ቦታ ተጋዘ። ካቭካዝ በሁለተኛዋ ኤርማንያ ግዛት በጥቁር ባሕር አጠገብ የምትገኝ ወረዳ ናት። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በግዞት እያለ ከገድል ጽናት የተነሳ በ407 ዓ.ም ዐረፈ። በኋላ በ438 ዓ.ም በቅዱስ ፕሮክልዮስ ርእሰ ኤጲስ ቆጶሳት ትእዛዝ የቅዱስ ዮሐንስ ኤፈወርቅ አፅም ወደ ቁስጥንጥንያ እንዲመለስና በቅድስት ሶፍያ ቤተ ክርስቲያን እንዲያርፍ ተደርጎአል።

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ታላቅ መተርጕመ ቅዱሳት መጻሕፍትና እጅግ የተመሰገነ ሰባኪ ወንጌል ነበር። ከዚያም በላይ እጅግ የታወቀ ደራሲ ሰለ ነበር በልዩ ልዩ መንፈሳዊ ርእስ ብዙ መጻሕፍት ጽፎአል። ከጻፋቸውም ብዙ ድርሳናት መካከል ስለ ቅድስተ ቅዱሳን ድንግል ምርያም ክብርና ቅድስና የተናገረው ድርሳን ትልቁን ቦታ ይዞ ይገኛል። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ቅድስት ድንግልን እንዲህ ሲል አመስግኖታል፦ «እግዚአብሔር ቃል ነፍስን ሥጋን ካንቺ ነስቶ ሰው የሆነ፣ ሙሽራም ከጫጉላው እንዲወጣ ካንቺ የተገኘ (የተወለደ) ማርያም ሆይ ደስ ይበልሽ፣ የጠፋ በግ አዳምን የፈለገው፣ ባገኘውም ግዜ በትከሻው የተሸከመው እውነተኛ ቸር ጠባቂ ካንቺ ተወለደ ማርያም ሆይ! ደስ ይበልሽ፣ እግዚአብሔር በሲኦል የጣ

ላት የሔዋን ጽኑ ፍዳ ባንቺ የጠፋ ማርያም ሆይ፣ ደስ ይበልሽ፣ እግዚአብሔር በብሩህ ደመና ሆኖ ወደ አንቺ የመጣ፤ ባንቺም ያደረ ምድር ቅድስት ማርያም ሆይ! ደስ ይበልሽ፤ በቅዱሳን አድሮ የሚኖር እግ ዚአብሔር ቃል ካንቺ ተወልዶ የተገለጠ ማርያም ሆይ! ደስ ይበልሽ፤ ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የምንሰ ግድለት ቃል (ሎጎስ) ካንቺ ይወለድ ዘንድ የወደደ፣ ዓለም ሳይፈጠር የነበረ እግዚአብሔር አንቺን የወደ ደ ማርያም ሆይ! ደስ ይበልሽ፣ እኔ ሐዋርያ የሆንኩለት የጌታ እናቱ ማርያም ሆይ! ደስ ይበልሽ፤ ካንቺ ከተወለደ በኋላ ማህተመ ድንግልናሽን ያለመለወጥ የጠበቀውን አማኑኤልን የወለድሽ ማርያም ሆይ! ደስ ይበልሽ። የማኅፀንሽ መሠረት ሳይናወጥ ንጉሥ ክርስቶስን የወለደሽ ማርያም ሆይ፤ ክብር (ሰላምታ) ይገባ ሻል፤ ልዩ (ቅዱስ) መድኃኒታችንን በመውለድሽ እናትና አገልጋይ የተባልሽ ማርያም ሆይ! ክብር (ስላም ታ) ይገባሻል፤ እግዚአብሔር ከሥጋሽ ሥጋን፣ ከነፍስሽ ነፍስን ሲነሳ ጸጋን ሞገስን አግኝተሻልና ማርያም ሆይ! ክብር (ሰላምታ) ይገባሻል» (ሃይማኖተ አበው ዘዮሐንስ አፈወርቅ ምዕ. 66 ክፍል 26 ገጽ 252)።

## 4. ቅዱስ ፐሮክልዮስ

ቅዱስ ፕሮክልዮስ ወይም ኤራቅሊስ በ426 ዓ.ም የሲዚኩስ ሀገረ ስብከት (ኤፓርኪያ) ኤጲስ ቆጶስ ሆኖ ተሾመ፤ ቀጥሎም በ434 ዓ.ም የቁስጥንጥንያ ፓትርያርክ ሆኖ ተሾመ። በ438 ዓ.ም ቅዱስ ፕሮክልዮስ የቅ ዱስ ዮሐንስ አፈወርቅን አጽም ካረፈበት ቦታ በክብር ወደ ቁስጥንጥንያ እንዲዛወር አደረገ። በ431 ዓ.ም በኤፌሶን የንስጥሮስን ትምህርት ለማውገዝ ከተሰበሰቡት አበው መካከል ፕሮክልዮስ አንዱ ነበር። ቅዱስ ፕሮክልዮስስ በስብከተ ወንጌል አሰጣጥ እጅግ የሚማርክ ችሎታ ያለው ሰለ ነበር ሕዝበ ክርስቲያኑ ዳግ ማዊ ዮሐንስ አፈወርቅ እያሉ ይጠሩት ነበር። በ446 ዓ.ም ያረፈው ቅዱስ ፕሮክልዮስ ስለ ምስጢረ ሥጋ ዌና ሰለ ቅድስት ድንግል ማርያም ክብር ከተናገረው ቃለ ስብከት ከዚህ በኋላ ጥቂቱን ጠቅሰናልና እንመ ልከተው።

«ኦ ከርሥ ዘተጽሕፈ ውስቴታ መጽሐፈ ግእዛን እምግብርናት ከኵሉ ሰብእ፤ አ ከርሥ ዘተጸውረ ውስቴ ታ ንዋየ ሐቅል ዘይትቃወሞ ለሞት በእንቲአነ፤ ኦ ገራህት ዘሰረፀ ለነ እምኔሃ ዘርዐ ሕላዌ ዘእንበለ ዘርዕ ፤ ኦ መቅደስ ዘኮነ ባቲ እግዚአብሔር ካህነ ዘእንበለ ይፍልስ እምህላዌሁ አላ በሣህሉ ለብሰ ክህነተ በ ከመ ሲመቱ ለመልከ ጼዴቅ»፦ «ለሰው ሁሉ ከመገዛት የሚያወዛ የነጻነት መጽሐፍ የተጻፈባት ማኅፀን የ ምትደምቅ ናት፤ ስለ እኛ ሞትን የሚቃወም መሣሪያ (ንዋየ ሐቅል) የተቀመጠባት ማኅፀን ምንኛ ድንቅ ና ት፤ እግዚአብሔር ከባህርዩ ሳይለወጥ፣ እንደ መልከ ጼዴቅ ያለ ክህነትን ገንዘብ ያደረገ ካህን ሆኖ ያገለ ገለባት (ሰው የሆነባት) መቅደስ ምንኛ ድንቅ ናት…» እያለ አመስግኖአታል።

ቀጥሎም ይህ ቅዱስ አባት ስለ ቅዱስ ዮሴፍ በተናገረው ክፍል እንዲህ ብሎአል፦ «የታመነ፣ የከበረና የተመሰገነ ዮሴፍ የሚናገረውን እንወቅ። እርሱ በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ምርያም የሚፈጸመውን ምስጢር አላወቀም፤ አገልጋይ የሆነላት ምስጢር ምን እንደሆነ አላወቀም፤ ለእርሱ ከታጨችለት ከድን ግል ነቢያት ሰለ እርሱ የተነገሩለት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያለ ዘር እንዲወለድ አላወቀም፤ በነቢያት እንደ ተነገረ ሕጻን ያለ አባት ከድንግል እንዲገኝ አላወቀም። ከንጹህ ዘር የተፈጠረች ድንግል የእግዚአ ብሔር ማደርያ እንድትሆን አላወቀም፤ ዘላለም መለወጥ የሌለበት ዳግማዊ አዳም ክርስቶስ ገነት ከምት ባለው ከድንግል እንዲገኝ አላውቀም። ከንጹሕ ዘር የተፈጠረች ድንግል የእግዚአብሔር ማደሪያ እንድ ትሆን አላውቀም፤ ዘላለም መለወጥ የሌለበት ዳግማዊ አዳም ክርስቶስ ገነት ከምትባለው ከድንግል ማር ያም እንዲወለድ አላወቀም፤ ፍጡራንን ሁሉ የፈጠረ ክርስቶስ ከእርሷ ያለ ዘር እንዲወለድ አላወቀም.. ያለ ዘር የጸነሰች የድንግልን የሆድዋን መግፋት ባየ ጊዜ የዮሴድ ልቡ አዘነ፤ የንጽሕተ ንጹሐንን የመቤ ታችንን ምስጢሯን ፈጽሞ መረመረ፤ በማያውቀው ምስጢር (የመንፈስ ቅዱስ ምስጢር) ፀንሳ ሲያገኛት ዮሴፍ በጽኑ አሳብ በማውጣት በማውረድ (በመዋግደ ሕሊና) ተያዘ፤ (ከእርሷ የሚወለደው በመንፈስ ቅ ዱስ ነውና አንተም እንደምትጠራጠረው  አይደለምና ዮሴፍ ሆይ አትፍራ) ብሎ የእግዚአብሔር መልአ ክ እስኪነግረው ድረስ ድንግል በዘር የፀነሰች መሰሎት ዮሴፍ ተጠራጠረ።

«ዮሴፍ መልአኩ ተገልጦ ከነገረው ወዲህ ግን በመልአኩ ቃል አመነ፤ ለቅድስት ድንግል ሰገደ፤ በንጽህ ናዋም አመነ፤ ነቢዮ ኢሳይያስ፦ «እነሆ ድንግል ትጸንሳለች፣ ወንድ ልጅም ትወልዳለች፤ ስሙም አማኑ ኤል ይባላል፤ ትርጋሜው እግዚአብሔር ከእኛ ባህርይ ጋር አንድ ሆነ ማለት ነው) ብሎ የተናገረላት ድን ግል እርሷ እንደ ሆነች አወቀ» ሲል ቅዱስ ፐሮክልዮስ ተናግሮአል (ሃይማኖተ አበው ዘኤራቅሊስ ምዕ. 48፤ ክፍል 4 እና 8፤ ገጽ 156 - 158)።

ከዚህ በላይ እንደ ተመለከትነው ቅድስት ድንግል ማርያም በቤተ ክርስቲያን አባቶችና መምህራን አንደበ ት በየጊዜው ተመስግናለች፤ በመላእክትና በነቢያት፣ በሐዋርያትና በሊቃውንት አንደበት እንደ ተመሰገነ ች፣ ቅዱስ ሕርያቆስ፦ «ኦ ድንግል.. በከመ ተብህለ ካህናት ወሊቃነ ካህናት ወደሱኪ» ብሎ እንደ መሰ

ከረላት በካህናት፣ በሊቃነ ካህናትና በምእመናን፣ እንደበት እስከ ዕለተ ምጽአት ስትመሰገን ትኖራለች። (ቅዳሴ ማርያም ዘደረሰ አባ ሕርያቆስ ቁ. 43)።

__ሰ. ዘለዓለማዊ ድንግልና__

ቅድስት ድንግል ማርያም በቅዱስ ገብርኤል ብሥራት እግዚአብሔር ቃልን ማለት አምላክን በድንግልና ከፀነሰች በኋላ፣ ከቅድስት ኤልሳቤጥ በተገናኘች ጊዜ ከቅድስት ኤልሳቤጥ የቀረበላትን ምስጋና አዳምጣ እግዚአብሔርን አመሰግናለች። እግዚአብሔርን ባመሰገነችበትም ቃል፦ «እነሆ ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ያመሰግኑኛል (ብፅዕት ይሉኛል)»፤ «እሰመ ገብረ ሊተ ኃይላተ ዐቢያተ»፦ «እርሱ ታላቅ ሥራ ሰርቶልኛልና» ብላለች። ኃይላተ ዐቢያተ ሲል፤ ታላላቅ ሥራዎችን ሰርቶልኛልና ለማለት ነው (ሉቃ. 1፤49)።

እግዚአብሔር ለቅድስት ድንግል ማርያም ያደረገላት ድንቅ ድንቅ ሥራዎች ብዙ ናቸው፤ ከእነዚያ ድንቅ ድንቅ ሥራዎች መካከል አንዱ ንጽሕና ነው። ይኸውም፦
«ሀብተ ንጽሕ ነው) ስትወልድ ጀምራ ንጽሕት መሆን ነው፣
«ንጽሐ ሕሊና» በሐሳብ ንጹሕ መሆን፣
«ንጽሐ ሥጋ» በሥጋ ንጹሕ መሆን፣
«ንጽሐ ልቡና» በልብ ንጹሕ መሆን ነው።

ከዚህም ጸጋ የተነሳ ለድንግል ማርያም፦ «ድንጋሌ ሥጋ»፣ «ድንጋሌ ሕሊና»፣ «ድንጋሌ ልቡና» ሰለ ተሰጣት፣ ሁል ጊዜ (ዘወትር) ድንግል ናት። «ቅድመ ፀኒስ»፣ ጌታን ከመጽነሷ በፊት፣ «ጊዜ ፀኒስ»፣ ጌታን በፀነሰች ጊዜ፣ «ቅድመ ወሊድ»፣ ጌታን ከመውለድዋ በፊት፣ «ጊዜ ወሊድ»፤ ጌታን በወለደች ጊዜ፣ «ድኅረ ወሊድ»፤ ጌታን ከወለደች በኋላ ምን ጊዜም በድግልና የጸናች ናት። ቅድስት ድንግል «ጌታ ታላቅ ሥራ ሠርቶልኛል» ያለችው አንዱ ጸጋ በድንግልና ጸንቶ መኖር ነው።

ቅዱስተ ቅዱሳን ማርያም ጌታችንን በድንግልና ጸንሳ በድንግልና ከመውለድዋ በፊት ድንግል መሆንዋን ትውልድ ሁሉ ያምናል። ነገር ግን ሐራጥቃዎች ማለት መናፍቃን በኋላ ዘመን ተነስተው በልባቸው ምኞት እየተመሩ (እየተሳቡ) (2ኛ ጴጥ. 3፤3) የቅድስተ ቅዱሳንን ዘለዓለማዊ ድንግልና በመካድ በማቴዎስ ወንጌል 13፤53-57 ላይ የተወሱት የዮሴፍ ልጆች ከእሷ እንደ ተወለዱ ያሰተምራሉ፤ በዚህም ራሳቸው ሰተው ሌላውን ያሰታሉ። ይኸውም የቅድስት ድንግልን ዘለዓለማዊ ድንግልና መካድና፣ ጌታችንን የተሸከመ ማኅፀን ፍጡራን ልጆች ተወልደውበታል ብሎ ማሰተማር በቀጥታ የጌታችንን አምላክነት መካድ ነው።

ነገር ግን ምስጋና ይግባውና ከቅድስት ድንግል ማርያም የተወለደው ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለም ሳይፈጠር የነበረና ዓለማትም በእርሱ የተፈጠሩ መሆናቸውን መጽሐፍ ቅዱስ በየምዕራፉ ይመሰክራል። ጌታችን በእውነት ቡሩክ አምላክ መሆኑን ቅዱሳን ሐዋርያት አስትምረዋል(ሮሜ 9፤5 ፣ቲቶ 2፤13 ፣1ኛ ዮሐ.5፤20)።

ከቅድስት ድንግል ማርያም የተወለደው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ መሆኑን የተረዱ ሰብአ ሰገል (የጥበብ ሰዎች) በቤተልሔም በሥጋ በተወለደ ጊዜ በኮከብ ተመርተው ጌታ ወደ ነበረበት ዋሻ (በረት) ገብተው ውድቀው ሰገዱለት፤ ለአምላክነቱና ለመንግሥቱ የሚገባውን መባዕ (እጅ መንሻ) አገቡለት።

ይኸውም ፍጹም አምላክ መሆኑን አምነው ዕጣን፣ የማይሻር ንጉሥ መኅኑን አምነው ወርቅ አቀረቡለት፣ ከኃጢአት በቀር ፍጹን ሰው መሆኑንም ተረድተው ከርቤ አቀረቡለት (ማቴ. 2፤10-12)።

ይህንን ቅዱስ ሥርዓት በመከተል የጥንቱንና ቀጥረኛውን ሃይማኖት የምንከተል ሁላችን ዕጣን ቋጥረን፣ መባዕ ይዘን፤ ብርንና ወርቅን ቋጥረን ወደ ቤተ ክርስቲያን እየሄድን፣ ለጌታችን እናቀርባለን። እግዚአብሔር ራሱም በነቢዩ አድሮ እንዲህ ብሎ አሰተምሮናል፦ «ከፀሐይ መውጫ ጀምሮ እስከ መግቢያዋ ድረስ ስሜ በአሕዛብ ዘንድ ታላቅ ይሆናል (ይመሰገናል)፤ በየሰፍራውም ለስሜ ዕጣን ያጥናሉ፣ ንጹሕም ቁርባን ያቀርባሉ፤ ሰሜም በአሕዛብ ዘንድ ከፍ ከፍ ይላል (ይመሰገናል)» (ሚል. 1፤11-12)።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ወልደ አምላክ (እግዚአብሔር ወልደ እግዚአብሔር) መሆኑን አጋንንት እንኳን ሳይቀሩ አምነውታል (ማቴ. 8፤29)። በቅፍርናሆም የነበሩ ከሐድያን ግን ከአጋንንት ያነሱ ሆኑ፤ ጌታችንን ወልደ ጸራቢ፣ የጠራቢ ልጅ፣ የዮሴፍ ልጅ ብለው ነቅፈውታል። በመንቀፋቸውም ተሰናከሉበት (ማቴ. 13፤ 53-58)።

የእነዚያን ከሐድያን አባባል በመከተል በዘመናችን የተነሡ መናፍቃን በዮሐንስ ወንጌል 7፤3 ፣እንደዚሁ
ም በማቴዎስ ወንጌል 13፤ 53-58 ያለውን ቃል መሠረት አድርገው የቅዱስት ድንግልን ዘለዓለማዊ ድንግ
ልና በመካድ ያዕቆብ፣ ዮሳ፣ ስምዖን፣ ይሁዳ ከማርያም የተወለዱ ናቸው እያሉ ይስታሉ፤ ሌላውንም ያ
ስታሉ።

እንደ እውነቱ ከሆነ አበው «ጠላት ይቀባል ጥላት» እንዲሉ፤ ከላይ በተገለጸው መሠረት «ወንድሞቹስ
ያዕቆብና ዮሳ ስምዖንም ይሁዳም አይደሉምን?» ብለው ከተናገሩት የጠላት የነቀፋ ቃል በቀር ሌላ ማሰረ
ጃ የለም፤ በስም የተቀጠሱት የጌታ ወንድሞች የተባሉ ሰዎች ከኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በኋላ ከድንግል
ማርያም መቼ እንደ ተወለዱ፣ በየት እንደ ተወለዱ፣ ከእነሱ መካከልም አሰቀድሞ ማን እንደ ተወለደ
የሚናገር አንዱም የጹሑፍ ማሰረጃ የለም። ከሐድያኑም ቢሆኑ በጠላትነት በቅድስት ማርያም ድንግልና
ተነሳስተው በግምት ከመንቀፍ በቀር አንድም የጽሑፍ ማሰረጃ አያቀርቡም፤ እንዲህ ያለ አፍራሽ ጽሑፍ
ም ተጽፎ አያውቅም። ሰለዚህ «ወንድሞቹ» በሚለው ቃል ምክንያት ብቻ በመመራት በስም የተጠቀሱት
ስዎች ከድንግል ማርያም የተወለዱ ናቸው ብሎ መናገር ፍጹም ሰሕተት ብቻ ሳይሆን ዐቢይ ኃጢአት ነ
ው።

የቅፍርናሆም ከተማ ነዋሪዎች ጌታችንን በሐሰትና በጠላትነት ተነሳስተው «ይህ የጠራቢ የዮሴፍ ልጅ አ
ይደለምን? ወንድሞቹስ ያዕቆብ፣ ስምዖን፣ ዮሳና ይሁዳ አይደሉምን?» ብለው በመሳደባቸው ከእውነተኛዋ
ሃይማኖት ወደቁ፤ ሰለዚህም በወንጌሉ «ተሰናከሉበት» ተብሎ ተጽፎአል (ማቴ. 13፤56)። ይህም ማለት
ቀናውን እምነት ትተው ሐሰቱን ሰለ ተከተሉ በክህደት እንቅፋት መሰናከላቸውን ለማመልከት ወንጌላዊ
ው «ተሰናከሉበት» አለ። አሁንም ከእውነተኛዋ ሃይማኖት በክህደት ተደናቅፈው የወደቁትን ወገኖች አ
ባባል የሚከተሉ ሁሉ በኃጢአት ይወድቃሉ።

በእርግጥ አረጋዊው ስምዖን በትንቢቱ እንደ ተናገረው (ሉቃ. 2፤33)፣ ከእስራኤል ልጆች ወገን ጌታችን ለ
ብዙዎቹ ለመውደቃቸውና ለመነሳታቸው ምልክት ነው። ማለትም ጌታችንን ለሚያምኑና ለሚከተሉ፣ ፍጹ
ም አምላክ መሆኑን ለሚመሰክሩ ሕይወታቸውና ትንሣኤያቸው ሲሆን፣ ለሚክዱት ግን የሚያደናቀቅፍና
የሚጥል የመንገድ ድንጋይ ነው (ማቴ.21፤44)። ቅዱስ ጴጥሮስም እንዳለው፣ «እርሱ ጌታችን የማዕዘን
ራስ የእንቅፋትም ድንጋይ፣ የማሰናከያም ዓለት ነው፤ የሚያምኑ ሰለ ሆኑ በቃሉ ይሰናከሉበታልና፣ ለዚህ
ደግሞ የተመደቡ ናቸው» ብሎአል (1ጴጥ. 2፤6-8)።

ሌላው ማሰተዋል የሚገባው ነገር ደግሞ፣ ከክርስቶስ ልደት በኋላ ከድንግል ማርያም የተወለዱ ልጆች
ቢኖሩ ኖሮ ጌታችን በተሰቀለ ጊዜ ቅድስት ድንግል በልጅዋ በኢየሱስ መሰቀል አጠገብ ቁማ ሰታለቅስ አ
ንዱ እንኳን ለምን ከአጠገብዋ አልተገኘም? ቅዱስ ዮሐንስ ከቅድስት ድንግል ጋር በጌታችን መሰቀል አ
ጠገብ ቆሞ ሲገኝ፣ ከድንግል ማርያም የተወለዱ የኢየሱስ ወንድሞች ቢኖሩ ኖሮ ምነው ከወንድሞቹ አ
ንዱ እንኳ በመሰቀሉ አጠገብ ቆሞ አልተገኘም? ይልቁንም መናፍቃኑ እንደሚሉት ቢሆን ኖሮ ጌታችን ቅ
ድስት እናቱን ለደቀ መዝሙሩ ለዮሐንስ «እነኋት እናትህ»፣ ለእሷም ቅዱስ ዮሐንስን «እነሆ ልጅሽ»
ብሎ ለምን ተናገረ? መልሱ ቅድስት ድንግል ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር ሌላ ልጅ ሰላልነበራት፣ ለዘለዓለ

ምም ድንግል ሆና እንደምትኖር ትንቢት ሰለ ተናገረላት (ትን. ሕዝ. 44፤1-4) ምንም ልጅ አልነበራትም።
እንዲህ ብሎ መናገሩ ቀርቶ ማሰቡም ዐቢይ ኃጢአት መሆኑን መገንዘብ ይገባል (ዮሐ. 19፤25-27)።

መናፍቃኑ እንደሚያወሩት ያዕቆብና ይሁዳ ከቅድስት ድንግል ማርያም የተወለዱ ቢሆኑ ኖሮ ሁለቱም በ
ጻፉአቸው መልእክታት ያዕቆብ በመጀመሪያው ምዕራፍ «ያዕቆብ የእግዚአብሔርና የኢየሱስ ክርስቶስ ባ
ሪያ» በማለት አይጽፍም ነበር። «የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ወንድም» ብሎ በጻፈ ነበር (ያዕ.1፤1)። ይሁዳ
ም እንዲሁ «የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ፣ የያዕቆብ ወንድም የሆነ ይሁዳ» ብሎ አይጽፍም ነበር። ነገር ግ
ን የኢየሱሰ ክርስቶስ ባሪያ የያዕቆብ ወንድም ብሎ ከመጻፍ የበለጠ ምን ማስረጃ አለ? (ይሁዳ 1፤1)።
ነገር ግን የማርያም ጠላቶች (ፀረ ማርያሞች) እንደሚያወሩት ሳይሆን፣ በማቴዎስ ወንጌል 13፤53-56 ላይ
የተጠቀሱት ያዕቆብ፣ ዮሳና ይሁዳ ከድንግል ምርያም የተወለዱ የኢየሱስ ወንድሞች ሳይሆኑ የሌላይቱ
ማርያም ልጆች እንደነበሩ ራሱ ቅዱስ ማቴዎስ መሰክሮአል። «ኢየሱስን እያገለገሉ ከገሊላ የተከተሉት
ብዙ ሴቶች በሩቅ ሆነው እየተመለከቱ በዚያ (በመቃብሩ) ነበሩ፤ ከእነርሱም መግደላዊት ማርያምና የያዕ
ቆብና የዮሳ እናት ማርያም፣ የዘብዴዎስም ልጆች እናት ማርያም ነበሩ» በማለት ጽፎአል (ማቴ. 27፤55)
። ቅዱስ ማርቆስም ሲመሰክር፣ «ሴቶችም ደግሞ በሩቅ ሆነው ይመለከቱ ነበር፤ ከእርሱም በገሊላ ሳለ
ይከተሉትና ያገለግሉት የነበሩ መግደላዊት ማርያም፣ የታናሹ ያዕቆብና የዮሳ እናት ማርያም ሰሎሜም ነ
በሩ» ብሎአል (ማር.15፤40-42)።

ስለዚህ የቅድስተ ቅዱሳንን ዘለዓለማዊ ድንግልና በመካድ መናፍቃን በግምትና በጠላትነት በመነሳሳት፣ «ድንግል ማርያም ኢየሱስን ከወለደች በኋላ ከዮሴፍ ልጆች ወልዳለች» ማለታቸው ቃላቅ ሰድብና ዐቢይ ክህደት ነውና ትምህርታቸውን በጥብቅ እናወግዘዋለን፤ ምእመናንም አጥብቀው እንዲቃወሙት እናሳስባለን።

ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ግን በእውነት ትንቢት የተነገረላት ጌታችንን ከመውለድዋ በፊትና ከወለደችም በኋላ ምን ጊዜም ንጽሕት ድንግል (ድንግል በክልኤ) መሆንዋን እናምናለን። ነቢዩ ሕዝቅኤል እንዳየው ሰማያዊ ራእይ፣ «ወደ ምሥራቅ ወደሚመለከተው በሰተውጭ ወዳለው ወደ መቅደሱ በር አመጣኝ፤ በሩም ተዘግቶ ነበር፤ እግዚአብሔርም ይህ በር ተዘግቶ ይኖራል እንጂ አይከፈትም፤ ሰውም አይገባበትም፤ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ገብቶበታልና ተዘግቶ ይኖራል» የሚል ነው (ሕዝ. 4 1-9) በእውነት ይህ ሰማያዊ ራዕይ በትክክል የቅድስተ ቅዱሳንን ዘለዓለማዊ ድንግልና ያመለክታል፤ ድንግል ማርያምም በንጽሕናና በድንግልና ዘለዓለም ጸንታ እንደምትኖር ያረጋግጣል።

የቤተ ክርስቲያን መምህራንም የነቢዩ ሕዝቅኤልን ራእይ መሠረት አድርገው የሚከተለውን ጽፈዋል። በሶስተኛው ዓለም አቀፍ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ በ431 ዓ.ም በኤፌሶን ከተሰበሰቡት ቅዱሳን አበው መካከል አንድ የሆነው የእንቁራ ሀገረ ስብከት ሊቀ ኤጲስ ቆጶስ የነበረው ቅዱስ ቴዎዶጦስ ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም ዘለዓለማዊ ድንግልና ሲመሰክር «እግዚአብሔር ከቅድስት ድንግል ተወልዶ ታየ፤ ድንግልም እንደ ቀድሞዋ በድንግልና ጸንታ ኖረች፤ እናትም ተባለች፤ ሕይወት የሚለውጥ እርሱ በድንግል ማርያም ተፈትሖ ማኅፀንን (ድንግልና ማጣትን) አላመጣባትም፤ ሕይወትንም የሚሰጥ እርሱ በድንግልና መውለድን አላስቀረባትም» ብሎአል፤ (ሃይማኖተ አበው ዘቴዎዶጦስ፣ ምእ. 53 ቁ 3 ገጽ )። ጨምሮም እንዲህ አለ፦ «ድንግል በድንግልና ሳለች እግዚአብሔር ከእርስዋ ተወለደ፤ ድንግል ማርያምን እናቴ አላት፤ እናት ብሎም ጠራት፤ ከፈጠራት ጀምሮ በምንም በምን አልተለወጠችም (ወኢረኩሰት በምንትኒ እምዘፈጠራ) ብሎአል ሃይማኖተ አበው ገጽ 174 ይመልከቷል።

5. <u>**ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ**</u>

ከ330 - 389 ዓ.ም የነበረው ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙም (በኋላ የቁስጥንጥንያ ርእስ ኤጲስ ቆጶሳት ሆኖ ተሹሞ የነበረው) ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም ዘለዓለማዊ ድንግልና በሰፊው ጽፎአል። ስለዚሁ በውጭ አገር ቋንቋ የተጻፈውን ትተን በአገራችን ቋንቋ ከተጻፈው ከሃይማኖተ አበው ቀጥለን እንጠቅሳለን።

«ሥጋ (ሰውነት) የሌለው እርሱ (እግዚአብሔር ቃል) ሥጋዋን ተዋሕዶ እንደ ሰው ሁሉ ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን በማኅፀንዋ ተወስነ፤ ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን ከተፈጸመ በኋላ የሚወለድበት ቀን ሲደርስ በማይመረመር ግብር (ሥራ) በሕቱም ድንግልና ተወለደ፤ ማኅተመ ድንግልናዋም አልተለወጠም፤ እሱ ማህተመ ድንግልናዋን ሳይለውጥ ተወለደ በወለደችም ጊዜ በወሊድ ጊዜ የሚሆን ምጥ ፈጽሞ አላገኛትም፤ የአምላክነት ሥራ ስለ ሆነ መፅነሷ በጣም ይደንቃል፤ የመውለድዋ ምስጢር ኃይልም አይመረመርም

፤ ማንም ማን ባሕርዩን የማያውቀውን እርሱን ወለደችው ማኅተመ ድንግልናዋም አልተለወጠም» (ሃይማኖተ አበው ምዕ. 8 ገጽ 212)።

በተጨማሪም ይህ ቅዱስ አባት ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም ዘለዓለማዊ ድንግልና ሲመሰክር (ወቦአ ቃለ እግዚአብሔር ውስተ ዓለም እምድንግልና ወላዲቱ፣ ወኢማሰነ በልደቱ ድንግልናሃ» «ቃል ከእናቱ በድንግልና ተወልዶ ወደዚህ ዓለም ገባ፤ በመወለዱም ድንግልናዋ አልተሰወጠም» በማለት አድረድቶአል (ሃይማኖተ አበው ገጽ 240)።
አክሎም ይህ ቅዱስ መምህር ስለዚሁ ሲያስረዳ፣ እንዲህ ብሎአል «ወሶበሂ ወለደቶ ዐቀበ ድንግልናሃ ዘእንበለ ርኩስ፣ ከመ በፅንሳ መንክር ትኩን መራሒተ ለሃይማኖት ዐቢይ።» ይህም ማለት «ድንቅ(አሰደናቂ) በሆነው ጽንሳ ለእውነተኛዋ ሃይማኖት መሪ ትሆን ዘንድ በወለደችው ጊዜ ድንግልናዋን ያለ መለወጥ አጸና» ማለት ነው (ሃይማኖተ አበው ገጽ 240)።

ከ412 - 444 ዓ.ም የእስክንድርያ ርእስ ኤጲስ ቆጶሳት የነበረው ታላቁ የቤተ ክርስቲያን አባት ቅዱስ ቁርሎስም ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም ዘለዓለማዊ ድንግልና ሲመሰክር እንዲህ ብሎአል «ከአዳም የጎን አጥንት በተፈጠረች ጊዜ እናት ስላልነበረቻት ሔዋን የሴቶች ባሕርይ እንዳልጎደለባት፣ አዳምም የጎኑ አጥንት ስለ ተነቀለ ከቀደመው የሥጋ ፍጥረት እንዳልጎደለበት፣ እንዲሁ የአዳምን አባት በሥጋ በወለ

ደችው ጊዜ የማርያም ማኅተመ ድንግልናዋ አልጎደለም፤ አዳምን የጎኑ አጥንት በተነቀለ ጊዜ እንዳላሳ መመው፣ እንዲሁ የገሊላ ሰው የምትሆን ድንግል ማርያምን ማለት እመ አምላክን ሕማመ ወሊድ (ም ጥ) አላገኛትም እንዲህ እናምናለን እንዲህም እንታመናለን» (ጸሎተ ቅዳሴ ዘቅዱስ ቄርሎስ ቁጥር 98 ይመልከቱ)።

ከፍ ብለን እንዳነበብነው ከዘመነ ሐዋርያት ጀምሮ እስከ አምስተኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ የነበሩ የ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትና መምህራን ቅድስት ድንግል ማርያም ጌታችንን ከመውለድዋ በፊት፣ ከወለ ደችውም በኋላ ምን ጊዜም ንጽሕት ድንግል መሆንዋን በሚገባ መሰክረዋል ከአምስተኛው ክፈለ ዘመን መጨረሻ ጀምሮ እስካለንበት ዘመን የተነሱ ቅዱሳን አበውም መጽሐፍ ቅዱስንና የቤተ ክርስቲያንን አባ ቶች ተከትለው ቅድስት ድንግል ማርያም «ወትረ ድንግል» መሆንዋን ማለት ሁል ጊዜ (ምን ጊዜም) ድንግል መሆንዋን በሰፊው አስተምረዋል።

ስለዚህ በመጽሐፍ ቅዱስ «አባቶችህ የሠሩትን የቀድሞውን የድንበር ምልክት አታፍልስ» ተብሎ የተጻ ፈው (ምሳሌ 22፤28) ቅዱሳን ሐዋርያትና ቅዱሳን ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን የወሰኑትን ሃይማኖትና ያሰ ተማሩትን ትምህርት እንዳታፋልሱ (እንዳትለውጡ) ለማለት ሰለ ሆነ፣ ይህንን ቃል በመጣስ ሲወርድ ሲ ዋረድ የመጣውን የቤተ ክርስቲያንን ትምህርትና እምነትዋን ለማፋለስና ለመለወጥ የሚሮጡትን መናፍቃ ን የቤተ ክርስቲያን ልጆች የሆናችሁ ሁሉ በእምነታችሁ ጸንታችሁ በራችሁን እንድትዘጉባቸው አደራ እንላለን።

<u>ረ. አኃዊሁ ለኢየሱስ (የኢየሱስ ወንድሞች)</u>

ወንድሞቹ ሰለ ተባሉት ሰዎች መነሻው ያው ቅዱስ ወንጌል ነው በቅዱስ ዮሐንስ ወንጌልና በሌሎቹ የ ኢሱስ ወንድሞች በሚል ሐረግ ተመልክተው ወይም ተወስተው ይገኛሉ። ኢየሱስም ገና ለሕዝቡ ሲናገ ር፣ እነሆ እናቱና ወንድሞቹ ሊያነጋግሩት ፈልገው በውጭ ቆመው ነበር አንዱም «እነሆ እናትህና ወን ድሞችህ ሊያነጋግሩህ ፈልገው በውጭ ቆመዋል»አለው ኢየሱስ ግን ለነገረው ሰው መልሶ «እናቴ ማን ናት? ወንድሞቼስ እነማን ናቸው?» አለው እጁንም ወደ ደቀ መዛሙርቱ ዘርግቶ «እነሆ እናቴና ወንድ ሞቼ በሰማያት ያለውን ያባቴን ፈቃድ የሚያደርግ ሁሉ እርሱ ወንድሜ፣ እህቴም፣ እናቴም ነውና» አለ (ማቴ. 12፤46-50) በዮሐንስ ወንጌልና በሐዋርያት ሥራም ወንድሞቹ ተብለው ተጠርተዋል (ዮሐ.7፤3 ፣ የሐዋ. 1፤14)።

<u>**ጥያቄ፤**</u> ወንድሞቹ የተባሉት እነማን ናቸው? ከማንስ የተወለዱ ናቸው?

<u>**መልስ**</u>፤ የኢየሱስ ወንድሞች የተባሉት ያዕቆብና ዮሳ፣ ሰምዖንና ይሁዳ ናቸው። እናታቸውም ከሰባ ሁለ ቱ ደቀ መዛሙርት (አርድእት) አንዱ የሆነው የቀለዮጳ ሚስት ማርያም ናት። ሰለዚሁም ወንጌላውያኑ መሰክረዋል፤ ማቴ. 27፤55 ፣ ማር.15፤40 መመልከት ነው።

<u>**ጥያቄ፤**</u> በእናት ካልተናኙ እነሱ ወንድሞቹ ማለት የኢየሱስ ወንድሞች ተብለው ለምን ተጠሩ?

<u>**መልስ፤**</u> የታናሹ ያዕቆብ፣ የዮሳና የይሁዳ እናት ማርያም (ማር.15፤41) ልክ እንደ ኤልሳባጥና እንደ ሰ ሎሜ የድንግል ማርያም የቅርብ ዘመድ ወይም እኅት ሰለ ነበረች፣ በዚሁ ምክንያት የኢየሱስ ወንድሞ ች ተብለው ተጠሩ፤ ምክንያቱም በቤተ እስራኤል ባሕል የእህት ልጅ፣ የእኅት ልጅ፣ የወንድም ልጅና እንዲሁም ቅርብ ቤተሰብ የሆነ ሁሉ ወንድም፣ እኅት እየተባለ መጠራት የተለመደ ነውና። ለአብነት ያ ህል አብርሃምንና ሎጥን ብንመለከት፣ የአብራሃምና ሐራ የታራ ልጆች ነበሩ፤ ሎጥ ደግሞ የአብርሃም ወንድም የሐራ ልጅ ነበር፣ ነገር ግን አብርሃም እንደ ተናገረው ሎጥና አብርሃም ወንድማማቶች እየተባ ሉ ይጠሩ ነበር (ዘፍጥ. 13፤8)። እንደዚሁም ሎጥ የአብርሃም ወንድም እየተባለ ይጠራ ነበር (ዘፍጥ.14 ፤16)።

በዚሁ ዓይነት ላባም የእኅቱ ልጅ ያዕቆብን «ወንድሜ» እያለ ይጠራው ነበር (ዘፍጥ. 29፤15)። በዚህ መሠረት ያዕቆብ፣ ይሁዳ፣ ዮሳና ስምዖን የቅድስት ድንግል ዘመድ የሆነችው የማርያም ልጆች ሰለነበሩ (ማር.15፤41) የጌታ ወንድሞች ተብለው ተጠሩ።

የቤተ ክርስቲያናችን መምህራን ደግሞ ያዕቆብን የዮሴፍ ልጅ ይሉታል። የጌታችን ወንድም ተብሎ መ ጠራቱንም እንዲህ ብለው ይገልጹታል ያዕቆብና ጌታችን በድንግል ማርያም በኩል በሥጋ ይዛመዳሉ፤ የዝምድናው መገናኛው አልዓዛር ነው፤ አልዓዛር ቅስራንና ማታያንን ይወልዳል፣ ቅስራ ኢያቄምን ይወል

ዳል፣ ኢያቄም ቅድስት ድንግል ማርያምን ይወልዳል፣ ማታያን ደግሞ ያዕቆብን ይወልዳል፣ ያዕቆብ ደግሞ ዮሴፍን ይወልዳል፣ ዮሴፍ ያዕቆብን ይወልዳል፤ በዚሁ ምክንያት እኁሁ ለእግዚእነ የጌታችን ወንድም ተባለ ይላሉ (መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፣ ቅዳሴ ሐዋርያት ቁጥር 16 ይመልከቱ)።

በመናፍቃኑ ዘንድ ግን ይህ ሁሉ ግንዛቤ የለም፤ ከቅዱሳን ሐዋርያትንና ቀጥለውም ቤተ ክርስቲያንን ሲያገለግሉና ትምህርተዋንም ሲያስፋፉ የነበሩትን አበው በቅድሚያ ማወቅና መከተል የለም ነገር ግን በራስ ብቻ በመመካትና «ምን አለበት» በማለት እንዲዚሁም በድፍረትና በግምት መጽሐፍ ቅዱሱን ሳይተረጉሙ በንባብ ብቻ ጥሬ ቃላቶችን በሰብከት መልክ በማቅረብ እናሰተምራለን እያሉ የመጽሐፍ ቅዱሱን ምስጢርና ዘይቤውን (አባባሉን) ይለውጣሉ። የጌታ ወንድሞች ተብለው ተጠርተዋልና ከድንግል ማርያም የተወለዱ ናቸው እያሉ በመደምደም ራሳቸው ተሳስተው ሌላውን ወደ ስሕተት አዘቅት ይጎትታሉ። ስለዚህ ምእመናን ሆይ! አሰተውሉ፣ ከመናፍቃን ክበብ ገለል በሉ።

## ሰ. የበኩር ልጅ

ወንጌላዊ ቅዱስ ማቴዎስ ኢየሱስ ክርስቶስን የቅድስት ድንግል ማርያም የበኩር ልጅ ይለዋል «ዮሴፍም ከእንቅልፉ ነቅቶ የእግዚአብሔር መልአክ እንዳዘዘው አደረገ፤ እጮኛውን ማርያምን ወሰደ፤ የበኩር ልጅዋንም እስክትወልድ ድረስ አላወቃትም» በማለት ጽፎአል (ማቴ. 1፤24-25) ቅዱስ ሉቃስም «የበኩር ልጅዋንም ወለደች፤ በመጠቅለያም ጠቀለለችው» ብሎአል (ሉቃስ 2፤7)።

እነዚህ «እጮኛ» «በኩር» «አላወቃትም» የተባሉ ቃላት በሃይማኖት ዓይን ካልታዩ፣ በአእምሮ መንፈሳዊም ካልተሰተዋሉ ነገር ግን ለዓለም የተለመደውን አስተሳሰብ በማሰብ ከተነበቡ ይቅርታ የሌለውን ኃጢአት ሊያሰከትሉ ይችላሉ ሰለሆነም የተነገሩትን ሀረጎች ወይም ቃላቶች መፍታት የሚገባ ነው። ለአብነት «እጮኛ» የሚለውን ቃል እንመልከት፤

«እጮኛነት»

1. በጋብቻ ሥርዓት አንድ ለመሆን የሚፈልጉ ሴትና ወንድ ከጋብቻቸው በፊት የሚፈጽሙት ውል ወይም ቃል ኪዳን መተጫጨት ይባላል።
2. አንድ ሰው ለትልቅ ሥራ ወይም ለሹመት ሲመረጥ «እጩ ሰው» «ለሥራ፣ ለሹመት የታጨ» ይባላል።
3. በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስና በምእመናን መካከል ያለው አንድነትም እጮኝነት በተባለው ቃል ይገልጻል ቅዱስ ጳውሎስ ሰለዚሁ ሲያሰተምር «እሰመ ፈሀርኩክሙ ለአሐዱ ምት ድንግል ወንጹሕ ክርስቶስ» ሲል ተናግሮአል ማለት እናንተን ንጹሐና ድንግል ሰለሆነ ለአንድ ክርስቶስ ላቀርባችሁ አጭቻችኋለሁ ብሎአል (1ቆሮ. 11 2-3)።
4. ለክብር ለቅድስና መመረጥም መታጨት ይባላል፤ ይኸውም እግዚአብሔር ሰለ ኢየሩሳሌም ሲናገር፣ «እኔ ለክብር (ለቅድስና) አጭቼሽ ነበር ፣ አንቺ ግን ለዲያብሎስ ሆንሽ» ብሎአል (መቃብ. ቀዳ 12፤35)

   ሰለዚህ ቅዱስ ዮሴፍ የማርያም እጮኛ ተብሎ የተጠራው ጠባቂዋ፣ አገልጋይዋ ለማለት ነው በነቢዩ በኢሳይያስ «ድንግል በድንግልና ትጸንሳለች፤ ወንድ ልጅንም ትወልዳለች ሰሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች» ተብሎ የተነገረው ትንቢት (ኢሳ. 7፤14) ለቤተ እሰራኤል፣ ለቤተ አይሁድ ሊረዳቸው ሰላልቻለ ሰለዚህ ዮሴፍ የጋብቻ እጮኛ ሳይሆን የአገልግሎት፣ የሥራ፣ የጥበቃ፣ የክብር እጮኛ ሆናት ማለት ነው።

   ቅዱሳን የቤተ ክርስቲያን አባቶችም መንፈስ ቅዱስ የተገለጸላቸውን ምስጢር ተከትለው ያሰተማሩት በዚሁ መንገድ ነው ከእነርሱም መካከል ለአብነት ቅዱስ ሕርያቆስ ያሰተማረውን እንጠቅሳለን፤ «ኦ ድንግል አኮ ለዮሴፍ ዘተፍኃርኪ ለታቃርቦ፣ አላ ከመ ይዕቀብኪ ንጹሐ (ንጽሐ) ድንግል ሆይ! ለዮሴፍ የታጩሽ ለመገናኘት አይደለም፤ ንጹሕ ሆኖ (በንጽሕና ሆኖ) ሊጠብቅሽ ነው እንጂ» ብሎአል (ቅዳሴ ማርያም ዘአባ ሕርያቆስ ፣ ቁጥር 44)።

## «የበኩር ልጅዋን እስክትወልድ ድረስ»

«የበኩር ልጅዋን እስክትወልድ ድረስ» (ማቴ 1፣25) ተብሎ የተጻፈው ደግሞ ወንጌላዊው «በኩር» ብሎ በመጻፉ «ከኢየሱስ ክርስቶስ በኋላ ተከታይ ልጅ ከድንግል ማርያም ተወልዶአል» እያሉ መናፍቃን በድፍረት ይናገራሉ። በመሠረቱ ነገሩ እነሱ እንደሚሉት አይደለም። በእርግጥ «በኩር ልጅ» ማለት የመጀመሪያ ልጅ ማለት ነው። ነገር ግን «በኩር» (የመጀመሪያ ልጅ) ሁሉ በግድ ተከታይ አለው ማለት

አይቻልም። በዚሁ መሠረት ክርስቶስ የቅድስት ድንግል የበኵር ልጅ ነው። ማለት ተቀዳሚና ተከታይ የሌለው አንድያ ልጅ ነው።እንዲህም በመሆኑ ለእግዚአብሔር አብም የበኵር ልጅ ይባላል(ዕብ. 1፤6)። ተቀዳሚ ተከታይ የሌለው ማለት ነው። ቅዱስ ዮሐንስ እንደ መሰከረው፣ ክርስቶስ የአብ ወልድ ዋሕድ ማለት አንድያ ልጅ ነው (ዮሐ. 1፣8)፤ ዘለዓለማዊ ድንግልናን ለተጐናጸፈችው ለቅድስት ድንግል ማርያም ክርስቶስ ወልድ ዋሕድ ማለት (አንድያ ልጅ) ነው፤ ስለዚህ በማቴዎስ ወንጌልና በሉቃስ ወንጌል ክርስቶስ የቅድስት ድንግል ማርያም በኵር ልጅ ተባለ (ማቴ 1፣25 ፤ ሉቃስ 2፣7)።

## «እስክትወልድ ድረስ አላወቃትም»

ወንጌላዊው ቅዱስ ማቴዎስ ሲጽፍ ቅድስት ድንግል«የበኵር ልጅዋን እስክትወልድ ድረስ አላወቃትም» ያለው ከወለደችም በኋላ አላወቃትም ማለቱ መሆኑን መረዳት ይገባል። ምክንያቱም፤
1ኛ/ ዮሴፍ ለቅድስት ድንግል ማርያም ጠባቂዋ እንጂ - እግዚአብሔር ይቅር ይበለንና - ባልዋ አልነበረም። ምክንያቱም እስዋ ትንቢት የተነገረላት ምን ጊዜም ድንግል ናትና።

2ኛ/ «እስከ...ድረስ» የተባለው ቃል ደግሞ ገደብ ያለው ጊዜንና መጨረሻ የሌለውን ጊዜ እያመለከተ የሚነገር መሆኑን መገንዘብ ተገቢ ነው። ለአብነት፣ የያዕቆብ ልጅ ይሁዳ ምራቱ ትእማርን «ልጄ ሴሎም እስኪያድግ ድረስ ባባትሽ ቤት መበለት ሆነሽ ተቀመጪ» አላት (ዘፍጥ. 38፣11)። ይኸውም ሴሎም ለአቅመ አዳም እስኪደርስ ድረስ ጠብቂ፣ ጊዜው ሲደርስ ያገባሻል ማለቱ ነው። እዚህ ላይ «እስከ...ድረስ» የተባለው ቃል የተወሰነ ጊዜን ለማመልከት እንደ ተነገረ ይታወቃል።

በተጨማሪም የእግዚአብሔር መልአክ ለዮሴፍ በራእይ ተገልጦ ሕፃኑን ኢየሱስን እናቱን ወደ ግብፅ ይዞ እንዲሄድ ባዘዘው ጊዜ «እስክነግርህ ድረስ በዚያ ተቀመጥ» አለው። እንደ ተባለውም ዮሴፍ ሕፃኑንና ቅድስት ድንግልን ይዞ ሄሮድስ እስከ ሞተበት ድረስ በግብፅ ቈየ (ማቴ. 2፤14-15)።

«እስከ...ድረስ» የተባለው ቃል ያልተወሰነውን ጊዜና ገደብ የሌለውን ዘመን እያመለከተ ሲናገር ደግሞ እንዲህ ይላል «የሳኦል ልጅ ሜልኮል እስከ ሞተችበት ቀን ድረስ አልወለደችም» (ሳሙ.ካልዕ 6፤23)። እነሆ ከዚህ ላይ ሜልኮል እስከ መጨረሻ ዕድሜዋ ድረስ፣ እስከ ዕለተ ሞትዋ ቀን ድረስ (እስከ መጨረሻው ድረስ) አለመውለድዋን ያመለክታል። በዚሁ መንገድ ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ «እነሆ እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ» ሲል ነግሮአቸዋል (ማቴ. 28፤20)። ጌታችን ክብር ምስጋና ይግባውና ከዓለም ፍጻሜ በኋላ ከደቀ መዛሙርቱ ይለያል ማለት ከቶ አይቻልም፤ ክህደት ነውና። ነገር ግን እሱ ከዓለም ፍጻሜም በኋላ በሚመጣው ዓለም ለዘለዓለም ከእነሱ ጋር እንደሚኖር ራሱ አረጋግጦላቸዋል (ዮሐ. 12፤26)። ስለዚህ «የበኵር ልጅዋን እስክትወልድ ድረስ» ተብሎ የተጻፈው ዮሴፍ ጻድቅ ነበርና ቅድስት ድንግልን እስከ መጨረሻው ቀን ድረስ (እስከ እለተ ሞቱ ድረስ) አላወቃትም ማለት መሆኑን መረዳትና ማመን ይገባል። ቅድስተ ቅዱሳን ድንግልም እግዚአብሔር የመረጣትና መልዕልተ ፍጡራን፣ መትሕተ ፈጣሪ በመሆን ስለ ሰዎች ሁሉ ወደ እግዚአብሔር እንደምትማልድ ማመን ተገቢ ነው። ይህን በሚመለከት በአጭሩ ቀጥለን እንመለከታለን።

## ሸ. አማላጅነትዋ

እንደሚታወቀው ማማለድ ማለት ስለ ሌላው መጸለይ፣ ማስማር፣ የደረሰውን ችግር እንዲወገድ ማስደረግ ማለት ነው። በዚሁ መሠረት ከእግዚአብሔር በታች፣ ከቅዱሳን ሁሉ በላይ ከፍ ከፍ ያለችና የከበረች ቅድስት ድንግል ማርያም ከእግዚአብሔር በተሰጣት የማማለድ ሥልጣን «ሰአሊ ለነ ቅድስት» ፤ «ቅድስት ሆይ! ለምኚልን» እያሉ ለሚለምኑአት ሁሉ ከእግዚአብሔር ምሕረትን እያማለደችና እየለመነች እንደምታሰጥ ቀናውንና የተመሰገነውን ሃይማኖት የሚከተሉ ሁሉ ያምናሉ። ምክንያቱም ቅድስት ድንግል የእግዚአብሔር እናትና አገልጋይ በመሆንዋ ከሁሉም ቅዱሳን በበለጠ ለእግዚአብሔር ቅርብ ናትና ። ለአብነት በእግዚአብሔር ፊት የሚቆመው ቅዱስ ገብርኤል ለእግዚአብሔር ቅርብ በመሆኑ (ሉቃስ 1፤19) ምስጢረ ድኅነትን (ደኅንነትን) በድንግል ማርያም አማካይነት ለዓለሙ ሁሉ አውጀአል።

በዚሁ መንገድ በሥርዓተ ዓለምም (ምድርም) ቢሆን ለቤተ መንግሥቱና ለንጉሰ ነገሥቱ ቅርብ የሆኑ ማለት የቀረበ ዝምድና ያላቸው ሰዎች ሁሉ ስለ ተበደሉና ስለ ተቸገሩ ሰዎች ወደ ንጉሡ እየቀረቡ እንደሚያማልዱ የታወቀ ነው። ለምሳሌ የባቢሎን ንጉሥ የነበረው አርጤክስስ በዘመኑ የተፈጸመው ታላቅ ለአማላጅነት ታሪክ ቢጠቀስ የያዝነው ርእስ የበለጠ ሊያጎላው ይችላል።

ታሪኩ እንደሚነግረን በንጉሥ አርጤክስስ ዘመነ መንግሥት ብዙ አይሁዳውያን ከኢየሩሳሌም በምርኮ ወደ ባቢሎን ሄደው በዚያው ይኖሩ ነበር፤ አስቴርና ዘመድዋ መርዶክዮስም ደግሞ የቤተ መንግሥቱ ዘ

በኛ በመሆን ይኖሩ ነበር። ንግስት አስቴር አይሁዳዊት መሆንዋን ለንጉሱ በመጀመሪያ አልገለጸችለትም ነበር። በዚህ መካከል እንደ ጠቅላይ ሚኒስተር የሚቆጠር የንጉሥ አርጤክስስ ባለሟል የነበረ ሐማ የተባለ ሰው ነበር። ሐማ በመርዶክዮስ ምክንያት ባቢሎን የነበሩት የአይሁድ ዘሮች እንዲደመሰሱ ንጉሡን በማሳሳት አዋጅ አሳወጀ። አዋጁ የተፈጸመበትን ደብዳቤ በንጉሡ ትእዛዝ በየአውራጃው ተበተነ። ሐማ ግን መርዶክዮስን በስቅላት ለመቅጣት በአደባባዩ እንጨት አስተከለ።

የአቢካኤል ልጅ የነበረች ንግሥት አስቴር ግን አዋጁን ሰምታና ደብዳቤውን አንብባ እጅግ አዘነች፤ ሦስት ቀን ሙሉም የሐዘን ልብስ ለብሳ ጾመች፤ ስለ ወገኖችዋም ወደ እግዚአብሔር ጸለየች፤ ቀጥላም ወደ ንጉሱ ወደ አርጤክስስ ገብታ ሕዝበ አይሁድን ለመደምሰስ በሐማ አማካይነት በሱሳ ግንብ የታወጀውን አዋጅ ለማስለወጥ ንጉሡን ተንበርክካ ለመነችው። ንጉሡም የአስቴርን ምልጃና ልመና ተቀበለ። ስለዚህም ቀደም ብሎ የታወጀውን የሞት አዋጅ ተሽሮ በምትኩ በግዛቱ ለሚኖሩ አይሁድ ሁሉ በንጉሡ ትእዛዝ የምሕረት፣ የሕይወትና የደኅንነት አዋጅ ታወጀላቸው። ሕዝበ አይሁድን ለመደምሰስና መርዶክዮስን በስቅላት ለመግደል የወሰነው ሐማ ግን ለመርዶክዮስን መስቀያ ተብሎ ተብሎ በአደባባዩ ተተክሎ በነበረው ዕንጨት ላይ በንጉሡ ትእዛዝ ተሰቀለና ሞተ (መጽሐፈ አስቴር 3፤10)።

ከዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የምንማረው በአንድ በኩል በንጹሕ ሰው ላይ ክፉ ሥራ የሚሠራና ለመሥራትም የሚያስብ ሁሉ እሱ ባሰበው መጥፎ ሥራ ራሱ እንደሚጠፋ ነው። በሌላው በኩል ደግሞ ንግስት አስቴር ንጉሡን ለምና ሕዝበ አይሁድን ማለት ወገኖችዋን ከእልቂትና ከድምሳሴ ማዳንዋን እንረዳለን። በዚሁ መንገድ የሰማይና የምድር መንፈሳዊት ንግሥት የሆነችው ቅድስተ ቅዱሳን ድንግል ማርያም በእናትነት ርኅራሔዋ ንጉሥ ክርስቶስን እየለመነችና እያማለደች ሥርየትንና ምሕረትን እንደምታሰጥ የታመነ ነው።

ከነቢያት መካከል ሙሴ ለእግዚአብሔር እጅግ የቀረበ ነቢይ ነበር፤ ሙሴ እጅግ ትሑት ሰው እንደ ነበር መጽሐፍ ቅዱስ ይመሰክርለታል (ዘኍል. 12፤3)። «እግዚአብሔርን ፊት ለፊት እንዳወቀው እንደ ሙሴ ያለ ነቢይ አልተነሳም» ዘኍል. 34፤10)። እግዚአብሔርም ስለ ሙሴ «ባሪያዬ ሙሴ እንዲህ አይደለም፤ እርሱ በቤቴ ሁሉ (በሕዝቤ ሁሉ) የታመነ ነው፤ እኔ አፍ ለአፍ በግልጥ እነጋገረዋለሁ፣ በሌላም አይደለም» ብሎ በአሮንና በእኅቱ በማርያም ፊት መስክሮለታል (ዘኍል. 12፤8)። ስለዚህ ሙሴ ወደ እግዚአብሔር እየጸለየና እያማለደ ሕዝበ እስራኤልን ከጥፋት አድኖአል።

ሙሴ ሕገ እግዚአብሔር ከራሱ ከእግዚአብሔር ለመቀበል ወደ ደብረ ሲና ወጥቶ በዚያ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት በጾምና በጸሎት በቆየበት ጊዜ ሕዝበ እስራኤል አሮንን በማስገደድ ጣዖትን አቁመው አምልኮ ባዕድን በፈጸሙ ጊዜ እግዚአብሔር ተቆጥቶ ሙሴን ጠርቶ «እነሆም አንገተ ደንዳና ሕዝብ ነው፤ እንዳጠፋቸው ተወኝ፤ አንተንም በረጋና በታላቅ ሕዝብ ላይ እሾምሃለው» አለው (ዘጸአ.32፤10)። ሙሴ ወደ እግዚአብሔር ተመልሶ «ወዮ እኒህ ሕዝብ ታላቅ ኃጢአት ሠርተዋል ለራሳቸውም የወርቅ አማልክት አድርገዋል፤ አሁንም ይህን ኃጢአታቸውን ይቅር በላቸው፤ ያለዚያ ግን እኔን ከጻፍከው መጽሐፍህ እባክህ ደምስሰኝ» አለው። በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር የሙሴን ጸሎትና ልመና ተቀብሎ ሕዝቡን ከመደምሰስ ተመለሰ (ዘጸአ.32፤14 ፣ 31-33)።

በዚሁ መሠረት ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ከሙሴ ይልቅ እጅግ የቀረበችና ከሙሴ ይልቅ እግዚአብሔር ያከበራት ቅድስተ ቅዱሳን ድንግል ማርያም ወደ እርስዋ ርዳታንና እገዛን ለሚፈልጉ ሁሉ ወደማይሻረው ዘለዓለማዊ ንጉሥ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ እየጸለየች እንደምታማልድ የተረጋገጠ ነው። ስለዚሁም በቃና ዘገሊላ ሠርግ ቤት ተገኝታ ያደረገችው ምልጃ ትልቁ ማስረጃ ነውና እሱን ቀጥለን እንመልከት።

## የቃናው ምልጃ

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በገዳመ ቆሮንቶስ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ከጾመ በኋላ ፈታኙን ዲያብሎስን ድል አድርጎ ወደ ገሊላ በተመለሰ በሦስተኛው ቀን፣ በገሊላ ቃና ከተማ ሠርግ ተደርጎ ነበር። ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ እንደ ጻፈው፣ ጌታችንና ደቀ መዛሙርቱ ወደ ሠርጉ ታድመው ነበር በዚያው ተገኝተው ነበር፤ ቅድስት ድንግልም ከጌታችን ጋር በሠርጉ እንደ ነበረች ወንጌሉ ያረጋግጣል። ሁሉም በዚያው ሳሉ እድምተኞቹ ሲመገቡና ሲጠጡ በድንገት ወይን ጠጅ አለቀ። በዚህ ጊዜ ቅድስት ድንግል ለልጅዋ «የወይን ጠጅ እኮ የላቸውም» አለችው። ኢየሱስም «አንቺ ሴት ካንቺ ጋር ምን አለኝ ጊዜዬ ገና አልደረሰም» አላት። እናቱም ለአገልጋዮቹ «የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ አለቻቸው። አይሁድም እንደሚያደርጉት የማንጻት ልማድ ስድስት የድንጋይ ጋኖች በዚያ ተቀምጠው ነበር፤ እያንዳንዳቸውም ሁለትና

ሦስት እንስራ ይይዙ ነበር። ኢየሱስም አገልጋዮቹን ጋኖቹን ውኃ ሙሉአቸው አላቸው። እስከ አፋቸው
ም ሞሉአቸው። አሁን ቀድታችሁ ለአሳዳሪው ስጡት አላቸው፤ ሰጡትም። አሳዳሪውም የወይን ጠጅ
የሆነውን ውኃ በቀመሰ ጊዜ ከወዴት እንደመጣ አላወቀም፤ ውኃውን የቀዱት አገልጋዮች ግን ያውቁ ነ
በር፤ አሳደሪውም ሙሽራውን ጠርቶ ሰው ሁሉ አስቀድሞ መልካሙን ወይን ያቀርባል፤ ከረኩ በኋላ ደ
ግሞ ጠንካራ ያልሆነውን ወይን ያቀርባል፤ አንተ ግን መልካሙን ወይን እስካሁን አቆይተሃል አለው።
ኢየሱስ ይህን ተአምር መጀመሪያ በገሊላ ቃና አደረገ፤ ክብሩንም ገለጠ፤ ደቀ መዛሙርቱም በእርሱ አ
መኑ» በማለት ወንጌላዊው ገልጾልናል (ዮሐ.2፣11)።

<u>**ጥያቄ፤**</u> ይህ በቃና ዘገሊላ ጌታችን ያደረገው ተአምር ለምን የመጀመሪያው ተአምር ተባለ?
<u>**መልስ፤**</u> ጌታችን ከገዳመ ቆሮንቶስ እንደ ተመለሰ የተአምራት ሥራ ማሳየት የጀመረው በዚያው በቃ
ና ተገኝቶ ውኃውን ወደ ወይን ስለ ለወጠው የመጀመሪያው ተአምር ተባለ። ጌታችን ልዩ ልዩ ተአም
ራት ያደረገው ከቃናው ተአምር በኋላ ነውና ስለዚህ የመጀመሪያው ተአምር ተባለ።

<u>**ጥያቄ፤**</u> አስደናቂው የቃናው ተአምር የተደረገው በማን አሳሳቢነት በማን አማላጅነት ነው?
<u>**መልስ፤**</u> ወደ ጌታችን ቀርባ «ወይን እኮ የላቸውም» ብላ በተናገረችው በቅድስት ድንግል ማርያም አ
ማላጅነት ነው።

<u>**ጥያቄ፤**</u> ውኃውን ወደ ወይን የተለወጠው በቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት ነው እንዳይባልማ
ራሱ ጌታ «አንቺ ሴት ካንቺ ጋር ምን አለኝ ጊዜዬ ገና አልደረሰም» ብሎ እንደ መለሰላት ተጽፎአል።
ታዲያ እንዴት በእሷ አማላጅነት ተፈጸመ ይባላል?
<u>**መልስ፤**</u> ጌታችን ቅድስት ድንግልን አንቺ ሴት ማለቱ ምንም ባንድ በኩል ልጅዋ ቢሆንም በሌላ በኩ
ል ጌታዋ፣ ፈጣሪዋ፣ አምላክዋ ስለ ሆነ እንደ አምላክነቱ አንቺ ሴት ብሎ ጠራት። በዚሁ መንገድ እግ
ዚአብሔር አዳምን በጠራ ጊዜ «አዳም ወዴት ነህ?» እንዳለው (ዘፍጥ.3፤9) ፤ አብርሃምን «አብርሃም»
ብሎ እንደጠራው (ዘፍጥ.12፤1) ቅድስት ድንግልንም «አንቺ ሴት» ብሎ በመጥራቱ «አላከበራትም ተ
ብሎ ሊታሰብ አይገባም። ምክንያቱም እሷ ፍጡር እሱ ደግሞ ፈጣሪ ነውና። በሌላ ጊዜም ጌታችን በ
ፊቱ ተከሳ ለቀረበችው ሴት «አንቺ ሴት የከሰሱሽ ወዴት አሉ?» ብሎ እንደጠየቃት እንመለከታለን (ዮ
ሐ. 8፣10)።

በሌላ በኩልም «ካንቺ ጋር ምን አለኝ» ብሎ ጌታችን በመናገሩ ጥያቄዋን እንዳልተቀበለና እንደ ቍጣ
ም የሚመስል አነጋገር እንደ ሆነ ሊገመት ይችል ይሆናል። ነገር ግን እንደዚህ አይደለም፤ አነጋገሩ አ
ሉታዊ አልነበረም፤ ቍጣም አልነበረም። እንደ እውነቱ ከሆነ ከኢየሱስና ከማርያም ጋር ምን ነበረ? ኢ
የሱስ የሚያውቀው ቅድስት ድንግል የማታውቀው ምን ነበረ? በተለይ የተቀመጠ ወይን ጠጅ ነበረ? አል
ነበረም። ወይም የሚበጠበጥ የወይን ጠጅ ድፍድፍ ነበረው? አልነበረውም። ስለዚህ በዚህ መልክ ኢየ
ሱስ «ካንቺ ጋር ምን አለኝ» ብሎ መመለሱ ትክክል ነበር።

በተለይም ጌታችን «ጊዜዬ ገና አልደረሰም» ያለው በሚገባ መገንዘብ ያስፈልጋል። ይኸውም «ጊዜዬ ገ
ና አልደረሰም» ማለት ተአምራት የምሠራበት ሰዓት ሥጋ ለብሼ (ተዋሕጄ) ወደዚህ ዓለም ከመጣሁ ወ
ዲህ አምላካዊ ተአምራቴን የምሠራበትን ጊዜ ገና አልደረሰም ማለቱ ነው። አባቶቻችን እንዳሉትም፣
ጌታችን ሥራውን የሚሠራበት ጊዜ አለውና፣ በቀትር የሚሠራውን በሠለስት (ሦስት) አይሰራውም፤ በሠ
ለስት የሚሠራውን በነግህ አይሠራውም። «ጊዜዬ ገና አልደረሰም» ማለቱ አንድም «ወይኑን ወደ ደም
ለውጬ ስለ ብዙዎች ኃጢአት ይቅርታ የሚፈሰው የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነውና ሁላችሁ ከእርሱ ጠ
ጡ ብዬ የምሰጥበት ሰዓት (ዕለተ ዓርብ) (ማቴ. 26፤ 27) ገና አልደረሰም» ማለቱ ነው ሲሉ ሊቃውንቱ
አመሥጥረውታል (ወንጌል ቅዱስ ንባቡና ትርጓሜው ዮሐ. 2፣4 ይመልከቱ)።

<u>**ጥያቄ፤**</u> ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለቅድስት ድንግል ካንቺ ጋር ምን አለኝ? ጊዜዬ ገና አልደረ
ሰም ብሎ በነገራት ጊዜ ቅድስት ድንግል ምን አለች? ወይም ምን አደረገች?

<u>**መልስ፤**</u> «ካንቺ ጋር ምን አለኝ» የሚለው የጌታ ቃል ለሰሚውና ለተመልካቹ የቅድስት ድንግልን ጥያ
ቄ ጌታችን እንዳልተቀበለው ይመስላል። ቅድስት ድንግል ግን ቃልዋን ጌታችን እንደ ተቀበላት ስላወቀ
ች፣ በቀጥታ አገልጋዮቹን (አሳላፊዎቹን) ጠርታ «ኢየሱስ የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ» አለቻቸው (ዮሐ.
2፤5)። አገልጋዮቹም የቅድስት ድንግልን ቃል ሰምተው ወደ ጌታ ሄዱ፤ ጌታችንም አገልጋዮቹን አይቶ
ለምን መጣችሁ ? ምን ትፈልጋላችሁ አላላቸውም። ነገር ግን «እነዚያን የድንጋይ ጋኖች ውኃ እየቀዳ
ችሁ እስከ አፋቸው ሙሉአቸው» አላቸው። አገልጋዮቹም ጌታችን እንዳዘዛቸው ስድስቱን ጋኖች ውኃ

ሞሉአቸው። እንደ ገናም ጌታችን አገልጋዮቹን «አሁን ቀድታችሁ ለአሳዳሪው (ለሠርጉ ኃላፊ) ስጡት»
አላቸው፤ እነርሱም ከውኃ ወደ ወይን የተለወጠውን ወይን ቀድተው ለአሳዳሪው ሰጡት፤ አሳዳሪውም
ወይኑን ቀምሶ አደነቀ ይላል።

ስለዚህ ከዚህ በላይ የተገለጸው የቃናው ተአምር የተደረገው በቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት መ
ሆኑን ማመን ይገባል። ነገር ግን «በእሷ አሳሳቢነት ማለት አማላጅነት አይደለም» ብሎ መከራከር በእ
ውነት ጨለማው ጨለማ አይደለም፣ ብርሃኑን ብርሃን አይደለም ብሎ እንደ መከራከር ነውና፣ ይህንን
እውነት ከማይቀበሉ ጋር መከራከር ፈጽሞ አያስፈልግም። ከመናፍቃን፣ ከሰነፎችና ካልተማሩ ሰዎች ጋ
ር መከራከር እንደማይገባ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ አስተምሮናልና (2ኛ ጢሞ. 2፤23)።

ርትዕት ስብሕት ማለት ቀጥ ያለችውንና የተመሰገነችውን ሃይማኖት (ኦርቶዶክስ ሃይማኖትን) ለምንከተ
ል ለእኛ ግን የቃናው የመጀመሪያው ተአምር የተፈጸመው (የተደረገው) በቅድስተ ቅዱሳን ድንግል ማር
ያም አማላጅነት መሆኑ እንደ ጸሐይ የበራ ሐቅ ነው። ይህንንም እውነት ተከትሎ በስድስተኛው ክፍለ
ዘመን የነበረው ኢትዮጵያዊው ቅዱስ ያሬድ በመንፈስ ቅዱስ ተገልጾለት ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም
የአማላጅነት ሥልጣን መስክሮአል፤ እንዲህ ሲል « ለሕዝብሽ (ለወገኖችሽ) የኃጢአት ይቅርታን ታሰ
ጪ ዘንድ፣ ዘለዓለማዊ ሕይወትን ለሚወርሱ ሁሉ መሸጋገሪያ ድልድይ ትሆኚ ዘንድ፣ ከአብ ከወልድ ከ

መንፈስ ቅዱስ (ከአንድ አምላክ) ተፈቅዶልሻል (ሥልጣን አግኝተሻል)» በማለት አመስግኖአታል (አንቀ
ጸ ብርሃን ናስተማስለኪን ይመልከቱ)።

ስለዚህ ቅድስት ቅዱሳን ድንግል ማርያም «ቅደስት ሆይ! ለሚኝልን» እያሉ ለሚማጸንዋት ሁሉ ምሕረ
ተ እግዚአብሔርን፣ ሥርየተ ኃጢአትን የምታሰጥ እውነተኛ አማላጅ መሆንዋን የሚያምን ሁሉ የተባረ
ከ ነው። ይልቁንም አንዳንድ ጊዜ እንደሚባለው ቅድስተ ቅዱሳን ድንግል ማርያም «በቀደመ ልመናዋ፣
በቀደመው አላማላጅነትዋ፣ በቀደመው ቃል ኪዳንዋ፣ በቀደመ ጸሎትዋ ታማልዳለች» እየተባለ እንደ
ሚነገረው ብቻ ሳይሆን እስከ ዕለተ ምጽአት ድረስ በመዓልትና በሌሊት በየቦታው «ቅደስት ሆይ! ለሚ
ኝልን» እያሉ ለሚለምንዋት ሁሉ ቅድስተ ቅዱሳን ድንግል ማርያም በየጊዜው እየጸለየችና እያማለደች
ከእግዚአብሔር ይቅርታና ምሕረትን እንደምታሰጥ በፍጹም ልባችን እናምናለን። እስዋንም «ደስ ይበል
ሽ» እያልን ይቅርታን እንድትሰጠን ወደ እርስዋ እንጸልያለን፤ እንዲህ እያልን፤-

«ድኅነተ ሥጋን፣ ድኅነተ ነፍስን እንድታሰጪ የምንለምንሽ ፤ ክብርን የተመላሽ ቅድስተ ቅዱሳን ድንግ
ል ማርያም ሆይ! ደስ ይበልሽ። ሁል ጊዜ ድንግል የምትሆኚ አምላክን የወለድሽ ቅድስተ ቅዱሳን ማር
ያም ሆይ! ኃጢአታችንን ይቅር ይለን ዘንድ ወደ ላይ ወደ ልጅሽ ወደ ወዳጅሽ ጸሎታችንን አሳርጊ።

«በእውነት ንግሥት የሆንሽ ንጽሕተ ንጹሐን ቅድስተ ቅዱሳን ድንግል ማርያም ሆይ! ደስ ይበልሽ። ንጽ
ሕተ ንጹሐን ቅድስተ ቅዱሳን ድንግል ማርያም ሆይ! የኃጢአታችንን ሥርየት ይሰጠን ዘንድ በልጅሽ በ
ክረስቶስ ፊት ለምኚልን።

«በእውነት ንግሥት የሆንሽ ንጽሕተ ንጹሐን ቅድስተ ቅዱሳን ድንግል ማርያም ሆይ! ደስ ይበልሽ። የባ
ህሪያችን መመኪያ ንጽሕተ ንጹሐን ቅድስተ ቅዱሳን ድንግል ማርያም ሆይ! ደስ ይበልሽ። አምላካችን
ን አማኑኤልን የወለድሽልን ንጽሕተ ንጹሐን ቅድስተ ቅዱሳን ድንግል ማርያም ሆይ! ደስ ይበልሽ። ለነ
ፍሳችን ይቅርታን ያደርግልን ዘንድ፤ ኃጢአታችንን ይቅር ይለን ዘንድ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፊት
እውነተኛ አስታራቂ ሆነሽ ታስቢን ዘንድ እንለምንሻለን (ሥርዓተ ቅዳሴ ቊጥር 155 ይመለከቷል)።

በረከተ ጸሎታ ውኩፈ ወሀብተ ረድኤታ ትሩፍ፤ ወምሕረተ ፍቁር ወልዳ ምልእተ አጽናፍ የሀሉ ምስለ
ኵልነ አግብርቲሃ ወአዕማቲሃ ለዓለመ ዓለም፣ አሜን።

በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ያለው የልመናዋ (የአማላጅነትዋ) በረከት፣ ፍጹም የሆነ የረድኤትዋ ሀ
ብት፣ ጽንፍ እስከ አጽናፍ የሞላው የተወዳጁ ልጅዋ ምሕረት (ቸርነት) በእውነት ከእኛ ከወንዶችም ከ
ሴቶችም አገልጋዮችዋ ጋር ለዘላለሙ ይሁን፣ አሜን፣ አሜን፣ አሜን።

አቡነ ገብርኤል
ክብረ ቅዱሳን በሚል ርእስ
በ1990 ካሳተሙት መጽሐፍ ላይ የተወሰደ።